| ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ<br>ኢየሱስ ክርስቶስ<br>ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ<br><u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u> | ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር<br>ድንግል ማርያም<br>እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ<br><u>ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u> |
|---|---|
| The Triumphant Lion of the Tribe of Judah<br>Jesus Christ<br>Eternal Priest in the Order of Melche-Zedeq the Ethiopian<br>King of Zion and King of Kings of Ethiopia | Ethiopia stretches out Her Hands to God<br>The Virgin Mary<br>Mother of God and Our Holy Mother<br>Queen of Zion and Ethiopia |

ቍጥር ፯/፳፻፯ ዓ. ም.

# ቃለ ዐዋዲ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የአዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤
አሓዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤

በስመ እግዝእትነ፥ ወእምነ፥ ወሃይማኖትነ፥ ወሀገሪትነ፥
ወንግሥትነ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤

በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ፥ ወአቡነ፥ ወመድኃኒነ፥
ወካህንነ፥ ወንጉሥነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡
ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ ማርያም ሥግው።

ማለትም፡-

በልዩ ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡
በእግዚአብሔር አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ስም፤

እናታችንና ሃይማኖታችን፥ አገራችንና ንግሥታችን
በኾነችው፡ አምላክን በወለደችው፡
በእመቤታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ስም፤

በአምላክነቱ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፥
በሰውነቱም፡ የማርያም ልጅ በኾነው፡
አባታችንና መድኃኒታችን፥ ካህናችንና ንጉሣችን
ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀሉ ኃይል።

\+ + +

**በአምላኬና በመድኃኒቴ በእግዚአብሔር አብ፥ በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፥ በሕይወቴና በፍቅሬ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ የኹለንተና ልጆቼ ለኾናችሁት፡ ለዓለሙ ሰዎች ኹሉ፡ ለወንዶቹም፡ ለሴቶቹም!**

**ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከሚለው፡ የመጀመሪያ መታወቂያችሁ ጋር፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የሚለውን የመጨረሻ ስም በመቀዳጀት፡ በስሜ፡ ተጠርታችሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ርስት ጕልቴ ለኾናችሁት፡ ለወንዶቹ ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያን እና ለሴቶቹ ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ልጆቼ በሙሉ!**

**በአንድ አምላካዊ ፈጣሪነቱ፥ በሥላሴነት መለኮታዊ ቸርነቱም፡ ሙሽራው፥ እናቱና መቅደሱ ባደረገኝ፡ በልዑል እግዚአብሔር ስም፡ ዘለዓለማዊው፡ የእናትነት ፍቅሬና ሰላሜ፥ በረከቴና ረድኤቴ፡ በያላችሁበት ይድረሳችሁ!**

## መግቢያ

ባለፈው፡ በ፷ተኛው አዋጅ፡ "እንግዴህ ወዲህ የምናገራችሁ እኔ ነኝ። የሚናገራችሁ፡ እርሱ፡ ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሢሕ ሳይኾን፡ እኔ፡ በትስብእት ስሜ፡ 'ድንግል ማርያም'፥ በእግዚአብሔራዊው ስሜ ደግሞ፡ 'ኢትዮጵያ' የምባለው ነኝ፡ የምናገራችሁ።" ብዬ በተናገርሁት፡ በዚያ ቃሌ መሠረት፡ አዎን! አኹን የምናገራችሁ፥ የማናግራችሁም፡ እናታችሁና ሃይማኖታችሁ፥ አገራችሁና ንግሥታችሁ፥ ክህነታችሁና መቅደሳችሁ፥ እመቤታችሁና ምድረ ርስታችሁ የኾንሁት፡ እኔ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እርሷም፡ እኔ ድንግል ማርያም ነኝ።

በዚህ አዋጅ የማሰማችሁ ቃሌ፡ ‹‹የወሊድ ቍጥጥር›› ተብሎ፡ ከአሕዛቡ ዓለም መንጭቶ፡ ‹ሕዝብ› በተባላችሁት *የፈጣሪ ወገኖች ዘንድ፥ በተለይም፡ ‹ክርስቲያን ነን›፣ ‹ቤተ ክርስቲያንም ነን›፣ ይልቁንም፡ ‹ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን› በምትሉት ልጆቼ ዘንድ ሳይቀር፡* ተስፋፍቶ ስለተሠራጨው፡ ሰብኣዊና ባዕድ ስለኾነው የኑሮ ፈሊጥ፡ በኪዳናውያንና በኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች በኩል፡ እየቀረበ ላለው ጥያቄ፡ መልስ የኾነውን መለኮታዊ ሥርዓት የያዘው መልእክት ነው።

ይህን፡ "የወሊድ ቍጥጥር" ምንነትና ማንነት፡-

በቅድሚያ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ ተመሥርቶ፥ ተገድግዶና ተደምድሞ፡ በሕያውነት በቆመው፡ በእያንዳንዳችሁ የተፈጥሮ አካላዊና ባሕርያዊ ሰውነታችሁ ውስጥ ባለው፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁና ምግባራችሁ፥ ሥርዓታችሁና ህልውናችሁ መነጽር፡ ጠልቃችሁ ልትመለከቱት፥ ልትመረምሩትም ይገባችኋል። በነፍስ አስተሳሰብ፥ በሥጋ አመለካከትና በመንፈስ ተመስጦ እየታየና እየተገመገመ እንደሚወሰነው፡ እንደማንኛውም ዓይነት ጽንሰ አሳብ፥ ወይም፡ ተግባራዊ አሠራር እና/ወይም ሚዛናዊ ፍርድ ኹሉ ማለት ነው።

ቀጥሎ፡ በኃይለኛውና በረቂቁ የመንፈስ ቅዱስ እሳት ምድጃችሁ፡ አቅልጣችሁና አንጥራችሁ በማውጣት፥ ፍጹም ፍትሓዊና ርትዐዊ በኾነው መለኮታዊ የፍርድ ሚዛናችሁም አጣርታችሁ፡ እውነተኛ ገጽታውን በማቅረብ፡ የእያንዳንዳችሁን ውሳኔ፡ በእየራሳችሁ ልትሰጡ ይጠበቅባችኋል።

ይህ፡ "የወሊድ ቍጥጥር" ነገር፡ እንደዓለማውያኑ ጉዳዮችና የአሠራር ልማድ፡ በማኅበር፥ በጉባኤ፥ በድምፅ ብልጫ የሚወሰን አይደለም። እግዚአብሔር፡ እንደማንኛውም መመሪያው፥ እንደማንኛውም፡ ሥርዓቱና እንደማንኛውም፡ እውቀቱ ኹሉ፡ ይህን፡ "የወሊድ ቍጥጥር" ነገርንም በሚመለከት፡ በእየአንዳንዱ ሰብኣዊ ፍጡራችን ልቦና ውስጥ፡ ግልጽ አድርጎ፡ በቃሉና በእጁ የጻፈው፡ መመሪያው፥ ሥርዓቱና እውቀቱ አለ።

ታዲያ! በየልቦናችሁ ሰሌዳ ላይ ተጽፎ የምታዩትና የምታነብቡት፡ ያ መለኮታዊ መመሪያ፥ ያ መለኮታዊ ሥርዓት፥ ያ መለኮታዊ እውቀት፡ ለእያንዳንዳችሁ፡ ምን ይላችኋል? መልሱ፡ እዚያው፡ በአንተም፥ በአንቺም፡ በሌሎቻችሁም ልቦና ላይ፡ በጉልህና በግዙፍ ተጽፎ፡ በግልጽ የምታዩትና የምታነብቡት ስለኾነ፡ እኔ፡ ለምን እነግራችኋለሁ? እናንተስ፡ እንዴት፡ የምትጠይቁት ይኾናል?

እስኪ፡ ይህንኑ መልስ፡ እኔም፥ እናንተም፡ ዐብረን እንየው! ዐብረንም እንመርምረው! ለእናንተ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ፡ ይህንና ይህን የመሰለውን ጉዳይ፡ ምንነቱንና ማንነቱን ለይታችሁ በምታውቁበት፡ ከላይ በተገለጠውና ፍቱን መሣሪያችሁ በኾነው፡ በቅዱሱ ኪዳን መነጽራችሁ፥ መመርመሪያችሁና መመዘኛችሁ፡ "ይህ፡ 'የወሊድ ቍጥጥር' ነገር፡ ከቶ ምንድር ነው? የእግዚአብሔር፥ ከእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ነወይ?" ብላችሁ፡ ለእየራሳችሁ ለምታቀርቡት ጥያቄ፡ የምታገኙት መልስ፡ ምንጊዜም ግልጽ ኾኖ ይቀርብላችኋል።

ይኸው፡ ለዚህ ጥያቄ፡ የሚሰሰጠው መልስ፡ "ይህ፡ 'የወሊድ ቍጥጥር'፡ ጽንሰ ሓሳብ፡ በሌላው፡ የእግዚአብሔር በኾነው ሥራ ላይ እየደረሰና እየተደረገ እንደሚታየው ኹሉ፡ ከሃይማኖት ጉድለት የተነሣ የመጣ ስለኾነ፡ የእግዚአብሔር፥ ከእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር አይደለም!" በሚል አጭር የድምዳሜ ቃል ተጠቃልሎ ይገለጻል።

"ጕድለቱ ደረሰበት!" የተባለውም ሃይማኖት፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ተመሥርቶና ከእርሱ መንጭቶ፡ በእግዚአብሔራዊው እውነትና እውቀት፥ እምነትና ሕይወት፡ ንጽሕናና ቅድስና፥ ግልጽነትና ፍጹምነት፡ እነሆ፡ ለ፯ሺ፭፻፯ (ሰባት ሽህ አምስት መቶ ሰባት) ዓመታት፡ በሕያውነትና በዘለዓለማዊነት ሲፈስስ የኖረውና የሚኖረው፥ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትም የምትመራበት፡ የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ ነው።

"ይህ፡ 'የወሊድ ቍጥጥር' ነገር፡ የእግዚአብሔር፥ ከእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ካልኾነ፡ ታዲያ! የማነው? መልሱ፡ "የዚያ፡ 'እባብ፥ ዘንዶ፥ ሰይጣን፥ ክፉ መንፈስ' የተባለው፡ የዲያብሎስ ነዋ!" የሚል ይኾናል።

ይህ እውነታ፡ የአብርሃም ልጅ የይስሓቅ ልጅ የያዕቆብ ልጅ የኾነው ይሁዳ፡ የወለዳቸው ወንዶች ልጆቹ፡ የሩካቤ ሥጋ ዘራቸውን፡ በ"ወሊድ ቊጥጥር" ዘዴ እንደሚደረገው ኹሉ፡ በሴት ማሕፀን እንዲዘራ ማድረግን "እምቢ!" ብለው፥ በምድር ላይ በማፍሰሳቸው፡ "ወእኩየ ኮነ፡ ውእቱኒ፡ ቅድመ እግዚአብሔር፤ እስመ ከመዝ ገብረ፤ ወቀተሎ ሎቱኒ።" ተብሎ እንደተጻፈ፡ ይህ ግብራቸው፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ ክፉ ኾኖ እንደተገኘባቸው፥ ከዚህ የተነሣም፡ እነርሱ፡ በሞት እንደተቀሠፉ፥ አውቃችኋል።

ደግሞም፡ ከዚያ ቀደም ብሎ፡ በሰዶምና ገሞራ ሰዎች ዘንድ እንደታየው፡ ዛሬም፡ በ"ወሊድ ቊጥጥሩ" ፈሊጥ እንደሚፈጸመው፡ ከተፈጥሮ ሥርዓት ውጪ የሚደረገው፡ የተመሳሳይ ጾታዎች ግብረ-ሰዶማዊ ኃጢኣታቸው፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ እጅግ በዝቶና ከብዶ፡ ጽዋውም ሞልቶ ስለፈሰሰ፡ እነዚያ ከተሞች፡ በእሳትና ዲን ተቃጥለው እንደተደመሰሱ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ተመዝግቦ ይነበባችኋል። ይኸውም፡ "ወአዝነመ እግዚአብሔር፡ ላዕለ ሰዶም፥ ወገሞራ፡ እሳተ፥ ወተየ፡ እምኀበ እግዚአብሔር፡ እምሰማይ። ወገፍትኦን ለእማንቱ አህጉር፥ ወለአድያሚሆን፥ ምስለ ኵሎሙ፡ እለ ይነብሩ ውስቴቶን፥ ወለኵሉ ዘርአ ምድሮሙ። ወነጸረት ብእሲተ ሎጥ፡ ድኅሬሃ፤ ወኮነት ሓውልተ ጼው።"

"እግዚአብሔርም፡ በሰዶምና በገሞራ ላይ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ፥ ከሰማይ፡ እሳትና ዲን አዘነበ፤ እነዚያንም ከተሞች፥ በዙሪያቸው ያለውንም አገር ኹሉ፥ በከተሞቹም የሚኖሩትን ኹሉ፥ የምድሩንም ቡቃያ ኹሉ ገለበጠ። የሎጥም ሚስት፡ ወደኋላዋ ተመለከተች፤ የጨው ሓውልትም ኾነች።" (ዘፍጥ. ፲፰፥ ፲፮-፴፫፤ ፲፱፥ ፩-፴፰፤ ፴፰፥ ፩-፴።)

ኹሉን ለመልካም የፈጠረው፥ እናንተም፡ በዚህ ማንነቱ ያመናችሁትና ያመናችሁበት እግዚአብሔር እኮ፡ "በአዳምነታችሁ፡ በመልኬ ፈጠርኋችሁ! በሥላሴነቴም፡ ከእኛ እንደአንዱ አደረግኋችሁ!" ያላቸውን፡ የመጀመሪያዎቹን ሰዎች፡ በወንድነት እና በሴትነት ጾታዎች፡ ለኹለት ከከፈላቸው በኋላ፡ እንደገና፡ በጋብቻ አንድነት አዋሕዶ፡ መሰሎቻቸው የኾኑትን፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን በመውለድ፡ እንዲባዙ ያደረገው፡ ለመልካም መኾኑን አውቃችኋል።

ታዲያ! ይህን እውነታ ካወቃችሁና ካመናችሁበት በኋላ፡ እንዴት፡ "የወሊድ ቊጥጥር" የተባለውን፡ ይህን የእግዚአብሔርን መልካም ፈቃድ የሚቃረን፡ ሰይጣናዊ ተግባር ትፈጽማላችሁ? እንኳንስ፡ በተግባር ልትፈጽሙት ይቅርና፡ አስባችሁ ልታቅዱትም እንኳ፡ አይገባችሁም።

በመሠረቱ፡ ያንን ክፉ ተግባር፡ አስባችሁና ዐቅዳችሁ የምትፈጽሙት፡ ካለማወቅ የተነሣ አይደለም፤ የእግዚአብሔር አብ መልኩ የኾነችው ነፍሳችሁ፡ መልካሙን የእግዚአብሔርን የሥነ ፍጥረት ሥርዓት፡ ኾነ ብላ፡ በመፃረር፡ ያንን ክፉ ተግባር፡ አስባና ዐቅዳ፡ በሥጋዊው አካሏና ባሕርይዋ የምትፈጽመው በመኾኑ ነው።

አዎን!  የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የኾነውና "ከእኛ እንደአንዱ ኾነች!" ያሰኛት መንፈሳዊው አካሏና ባሕርይዋ፡ የእግዚአብሔር ወልድ ክፍል በኾነው፡ በሥጋዊው የአካል እስትንፋሷና የባሕርይ ቃሏ መሣሪያነት ሳይቀር፡ አበክሮና አጠንክሮ የተናገራትን እኮ፡ ነፍሳችሁ፡ ሰምታ፡ በዓመፀኛነቷ ምክንያት፡ ከመቀበልና ከመፈጸም፡ "እምቢ!" በማለቷ ነው።

"እምቢ!" ያለችውም፡ መንፈሳዊው አካሏና ባሕርይዋ፡ ያን ፍጹም እውቀት ከገለጠላት በኋላ፡ አኹንም፡ ከነፍሳዊው የሃይማኖቷ ጉድለትና ከሥጋዊው የምግባሯ ድክመት የተነሣ፡ እርሱን፡ "አሻፈረኝ!" ብላ፡ በክህደት፥ በዓመፅና በአምልኮ አመንዝረኛነቷ የምትቀጥል በመኾኗ ነው።

ይህች ነፍሳችሁ፡ ምርጫዋ፡ እግዚአብሔርን የመምሰሉን ብቅዓት የምታገኝበትን፡ መንፈስ ቅዱሳዊውን አካሏንና ባሕርይዋን የኾነ እንደኾነ ግን፡ እግዚአብሔር፡ በመልካምነት የፈጠረውን፡ ማናቸውንም ነገርና የሠራውን ሥርዓት ኹሉ፡ መልካም መኾኑን በማመን፡ በመልካምነት የተፈጠረውን የውስጥ ባሕርያዊ ስሜቷን ጭምር፡ በመንፈስ ቅዱሳዊው የሃይማኖት ኃይል እየተቈጣጠረች ትፈጽማለች እንጂ፡ የፈጣሪዋን ፈቃድ የምትቃወም አትኾንም፤ አዎን! የእግዚአብሔር የኾነውን መልካሙን ነገርና ሥርዓት ለማፍረስ በሚሞክርና ፀረ እግዚአብሔር በኾነ፡ "ክፉ ሥራ" ላይ የምትሰማራ አትኾንም። እዚህ ላይ፡ ያ፡ "ክፉ ሥራ" የተባለው ግብር፡ ይህ የምንነጋገርበት፡ "የወሊድ ቍጥጥር" የተባለው ርእስ ነገር ነው።

በዚህ አንጻር፡ ነፍሳችሁ፡ "የወሊድ ቍጥጥር" በተባለው ክፉ ግብር ተጠምዳ፡ የቀንበሩ ተሸካሚና የልማዱ ባሪያ የምትኾነው፡ ምርጫዋ፡ እግዚአብሔርን ከሚያስመስላት፡ ከመንፈስ ቅዱሳዊው አካሏና ባሕርይዋ ውጪ አድርጎ፡ ሰይጣንን የሚያስመስላትንና ለእንስሳዊው ፍላጎቷ ተገዢነት የሚዳርጋትን፡ የሥጋዊ አካሏንና ባሕርይዋን ፈቃድ ፈጻሚ ስትኾን ነው።

በዚህ ረገድ፡ የእግዚአብሔር የኾነው፡ መልካሙ ነገርና ተፈጥሮአዊዉ ሥርዓት ምንድር ነው? "የወሊድ ቍጥጥር" የተባለውንስ፡ ተፃራሪና ሓሳዊ ነገር፡ ምን አመጣው? እንዲህ፡ አስፈላጊ ሊኾን የቻለበት መነሻ ምክንያትስ፡ ከቶ ምንድር ነው? ለእነዚህ ጥያቄዎች፡ መልስ የኾነውን ቍም ነገር፡ እስኪ፡ በእኔ በእናታችሁ ቃል በአጭር ሓተታም ቢኾን፡ ላብራራላችሁ!

## ቅዱሱ ኪዳን፡
## ስለወንድ ዘር እና ስለሴት ወርኀዊ አበባ የሚለው።

ቀደም ብዬ እንዳወሳሁላችሁ፡ የእግዚአብሔር የተፈጥሮ ሥርዓት የኾነው፡ የወንድና የሴት የሩካቤ ሥጋ ፍትወት [የሥጋ ግንኙነት ፍላጎት]፡ መልካም እንጂ፡ ክፉ አይደለም፤ ቅዱስ እንጂ፡ ርኩስ አይደለም፤ ጽድቅ እንጂ፡ ኃጢአት አይደለም።

አካሉና ባሕርዩ፡ በመሠረቱ፡ እንዲህ፡ በፍጹም መልካምነትና ቅድስና፡ ውበትንና ንጽሕናን የተቀዳጀ፥ መነሻ ምንጩና መድረሻ ግቡም፡ በፈጣሪ አካላዊ መልክና ባሕርያዊ ጠባይ፡ በመለኮታዊ ሥነ ጥበብ የተከናወነ፡ ሰብኣዊ ፍጡርን የሚያስገኝ አምላካዊ ሥርዓት ነው።

እውነታው፡ ይህ ኾኖ ሳለ፡ ይህ ኹሉ፡ ያማረና የጸዳ፡ ዕፁብ ድንቅ የመለኮት ሥራ፡ ከዚህ፡ ከእግዚአብሔራዊው የእውነት ምንነቱና ማንነቱ፡ ፈጽሞ ተቀይሮ፡ በዚያ፡ በክፉቱ ኃይል፡ "ኃጢኣት"፥ እርሱም፡ "እውነት የታጣችበት ሓሰት" የሚል የርኵሰት ስያሜ ተሰጥቶት፡ እንዴት፡ ወደሰይጣናዊው ሓሳዊ ምንነቱና ማንነቱ እንደተለወጠ መመልከቱ፡ እጅግ ያሳፍራል፤ ያስገርማልም።

ይኸውም፡ ቅዱሱ ፈጣሪ፡ በተቀደሰው የሥነ ፍጥረት ትንግርታዊ ጥበቡ፡ ፍጹም ቅዱስና መልካም አድርጎ የፈጠረውን አካልና የሠራውን ሥርዓት ተከትሎ፡ በተባዕቱና በእንስቲቱ፥ ማለትም፡ በወንዱና በሴቲቱ ሰውነት ውስጥ በሚነሣሣው ባሕርያዊ ፍትወት ምክንያት፡ ከወንዱ ጾታዊ አካል የሚፈልቀው ዘር፡ እንደአንዳች ክፉ ነገር ተቆጥሮ፡ እንዴት፡ ራሱ፡ "ኃጢኣት!" እንደተባለ፥ ዘሩን ለመቀበል፡ ከሴቲቱ ጾታዊ አካል የሚፈልቀው፡ የወር አበባም፡ እንዴት፡ "መርገም! ርኵሰት! ዐደፍ፥ ጕድፍ" እንደተባለ፥ ደግሞም፡ የወንዱ አባለ ዘር፥ የሴቲቱም ማሕፀን፡ ኹለቱም፡ "ኀፍረተ ሥጋ!" ፡ "የሥጋ ማፈሪያ!" የሚል የመታወቂያ ስያሜ ተሰጥቷቸው፡ እንዴት፡ እግዚአብሔራዊውን የክብር ማዕርጋቸውን ተገፍፈው፡ ወደሰይጣናዊው የውርደት ዐዘቅት ሊጣሉ መቻላቸው ነው።

ታዲያ! ይህ ይትበሃል፡ እግዚአብሔር፡ በንጽሓ ጠባይ፡ በመልኩ በፈጠረውና **"ናሁ አዳም ኮነ፡ ከመ አሓዱ እምኔነ፤ ያእምር ሠናየ፥ ወእኩየ!" "እነሆ፡ አዳም፡ መልካሙንና ክፉውን በማወቅ፡ ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!"** ባለው ሰውነት ውስጥ፡ "ኃጢኣትን ጨምሮ ነው የሠራው!" አያሰኝምን? አዎን! ያሰኛል። (ዘፍጥ. ፫፥ ፳፪።)

ይኹን እንጂ፡ እንዲህ እንዳይባል፡ ማንኛውም ሰብኣዊ ፍጡር፡ ሰውን ለአምላክነት ባበቃው፡ በጥንተ ተፈጥሮው ንጽሓ ጠባይ ጸንቶና ያን መርጦ እስከቀጠለ ድረስ፡ ክፉት፥ ኃጢኣትና ሞት ሊቀርቡት በማይቻላቸው፥ እግዚአብሔርንም በሚመስልበት ሕፃናዊ ሕይወት ሊኖር እንደሚችል፡ ኄኖክንና እኔን እናታችሁን፥ እኛንም የመሰሉትን ቅዱሳንንና ቅዱሳትን፡ ለአብነት ማዘከር ይቻላችኋል። ይህም እውነታ፡ ጥንት፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ እንደተረጋገጠው፥ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ አምነውበት፡ ሲከተሉትና ሲፈጽሙት በኖሩበት ሕይወት ገዝፎ ታይቷል።

ነገር ግን፡ ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር፡ እንደጾታው ዓይነት፡ ለዓቅመ አዳም ሲደርስ፥ ወይም፡ ለዓቅመ ሔዋን ስትደርስ፡ የግል ምርጫው፡ ይህ፡ የጽድቁ፡ እርሱም፡ የእግዚአብሔሩ እውነት መኾኑ ቀርቶ፡ ከዚህ ይልቅ፡ የኃጢአቱ፡ እርሱም፡ የዲያብሎሱ ሓሰት፡ በሚኾንበት ጊዜ፡ "ኃጢአተኛ"፡ እርሱም፡ "የእግዚአብሔርን እውነት ያጣ፡ ሓሰተኛ!" ተብሎ፥ ሰውን ለአምላክነት ያበቃውንና በጥንተ ተፈጥሮው የተቀዳጀውን፡ ያን ንጽሓ ጠባይ ተገፍፎ፥ የክፋት፥ የኃጢአትና የሞት ባሪያም ኾኖ፡ ዲያብሎስን በሚመስልበት ህልውና ይኖራል።

እግዚአብሔር፡ በንጽሓ ጠባይ፡ በመልኩ በፈጠረውና "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ባለው ሰውነት ውስጥ፡ ኃጢአትን ጨምሮ እንደፈጠረ የሚያስመስለውን፡ ይህን ክፉ አስተሳሰብ፡ በጽሙና ስታስቡትና በተመስጦ ስትመረምሩት፡ እጅግ እያስገረማችሁ፡ ሥጋዊውን ብቻ ሳይኾን፤ ነፍሳዊውንና መንፈሳዊውን ጭምር አጠቃልሎ፡ የሰዎች፡ የተፈጥሮ ሕዋሳት፡ ከትክክለኛ አገልግሎታቸው ውጪ ኾነው የተሰነካከሉ መኾናቸውን ታረጋግጣላችሁ።

ይኸውም፡ የመመልከቻ ዓይኖቻቸው፡ የቱን ያህል እንደታወሩ፥ የማወቂያ አእምሮዎቻቸውም፡ የቱን ያህል እንደደነዘዙ፥ የማስተዋል ኅሊናዎቻቸውም፡ የቱን ያህል እንደማሰኑ፡ ለመገመትም እንኳ ያዳግታችኋል። ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ወገኖችና አገልጋዮች፥ ተጠሪዎቹም ነን!" በሚሉት፡ በቤተ ክህነቱና በሃይማኖተኞቹ ድርጅቶች ዘንድ፡ የክፋቱ አበጋዝ የኾነው ዲያብሎስ፡ በዚህ ረገድ፡ የቱን ያህል እንደሠለጠነ፡ በገሃድ የሚያረጋግጥ ማስረጃን ያስጨብጣችኋል።

በእግዚአብሔር መልክ በተፈጠረው፥ ፈጣሪውም፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ባለው፡ በሰብአዊው ፍጡር ሰውነት ውስጥ፡ በሥላሴ የተዋሕዶ ምሥጢር፡ አንድ የኾኑት፡ የነፍስ፥ የሥጋና የመንፈስ፡ ሦስቱም አካላትና ባሕርያት፡ በራሱ፡ በእግዚአብሔር የተፈጠሩ፥ ከእርሱ የተገኙና የእርሱ የኾኑ መኾናቸው፡ በሥነ ፍጥረትም ኾነ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ የተረጋገጠ እውነት ኾኖ ሳለ፡ ነገር ግን፡ በክፋቱ ኃይል ማየል የተነሣ፡ ይህ ኹሉ የእግዚአብሔሩ እውነታ፡ በዚህ መልኩና ይዘቱ እንዳይታወቅ መደረጉ ያስደንቃል።

እውነታው፡ ይህ ከኾነ፡ ታዲያ! ከእግዚአብሔር አብ ባሕርይ ተከፍላ፡ የተፈጠረችው ነፍሳችሁ፡ ከንጽሓ ልቡና አካሏና ባሕርይዋ የሠረፀውን፥ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረውን፥ ፈጣሪውም፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ያለውን፡ ሰብአዊ ፍጡር ለማስገኘት የሚያስችላትን፡ የሩካቤ ሥጋ ፍትወቷን ለመፈጸም፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በኾነው፡ በመንፈሳዊው አካሏና ባሕርይዋ ስምምነት፥ የእግዚአብሔር ወልድ በኾነው፡ በሥጋዊው አካሏና ባሕርይዋ ዘር አማካይነት የምታካኺደው፡ እግዚአብሔራዊው የተፈጥሮ ሥርዓት፡ የተቀደሰው ረቂቁ ስሜትና ቅዱሱ ዘር ጭምር፡ "ጽድቅ" መኾኑ ቀርቶ፡ እንዴት፡ "ኃጢአት" ተብሎ ተሰየመ!? "ቅድስና" መኾኑ ቀርቶስ፡ እንዴት፡ "በኃጢአትነት" ተፈረጀ!?

ይህ ኹሉ ሓሳዊ ሙከራ፡ ሊደረግ ቀርቶ፡ ፈጽሞ ሊታሰብም የሚገባው አይደለም፤ ሰይጣናዊ ነውና።

ኃጢአትስ፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረውን፥ ፈጣሪውም፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ያለውን፡ ሰብኣዊ ፍጡር እንዲያስገኝ፡ እግዚአብሔር የሠራውን፡ ይህን፡ የተቀደሰ፡ ዕፁብ ድንቅ ሥርዓት፡ "ኃጢአት ነው!" ብሎ፡ "በኃጢአትነት" መፈረጅ ነው።

ኃጢአትስ፡ እግዚአብሔር፡ ለዚሁ ቅዱስ ዓላማው፡ ከግብ መድረስ፡ በዚሁ ሰብኣዊ አካልና ባሕርይ ውስጥ፡ በንጽሓ ጠባይ፡ ቀድሶና አንጽቶ፥ አስውቦና አጣፍጦ የፈጠረውን ዘርና የወር አበባ፡ "ኃጢአትና መርገም፥ ርኵሰትና ዐደፍ" ብሎ ማንቋሸሽና መስደብ ነው።

ኃጢአትስ፡ እግዚአብሔር፡ በጥንተ ተፈጥሮ፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ብሎ፡ በመልኩ ለፈጠረው ሰብኣዊ ፍጡሩ፡ መልካም የደስታ ሕይወት ይኾንለት ዘንድ፡ የሠራለት ሥርዓትና የሥርዓቱ አባላት፡ "ኃጢአት ናቸው!" ተብለው፡ በዚያ ሰውነት ውስጥ፡ የሌለ ስሜታዊ ጭራቅንና ምትሓታዊ ደዌን በማሳደር፡ ያን ሰው፡ ለማያቋርጥ ፍርሃትና ድንጋጤ፥ ጭንቀትና ሥጋት፥ ፈተናና ሥቃይ መዳረግ ነው።

ኃጢአትስ፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረውን፥ ፈጣሪውም፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ያለውን፡ ሰብኣዊ ፍጡር ያስገኙ ዘንድ፡ እግዚአብሔር የሠራውን፡ የተፈጥሮ ሥርዓት፡ "ኃጢአት ነው!" ብሎ፡ በኃጢአትነት በመፈረጅ፡ የሰው ወገኖች ኹሉ፡ ያን እግዚአብሔራዊ የኾነውን የተፈጥሮ ሥርዓት ተከትለው፡ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነታቸውን፡ ከፍትወት ተባባሪያቸው፡ ማለትም፡ ወንድ፡ ከሴት፥ ሴትም፡ ከወንድ ጋር ከማድረግ ይልቅ፡ "የወሊድ ቍጥጥር" ጠንቅን ያስከተለውንና ከጾታ መሰሎች ጋር፡ ግብረ ሰዶምን፡ በይፋና በሕጋዊነት እስከማካኼድ የሚያደርሰውን፡ ኢተፈጥሮአዊ፡ ማለትም፡ ከተፈጥሮ ውጪ የኾነውን፥ እንስሳት፥ አራዊትና አዕዋፋት እንኳ የማያደርጉትን አስጸያፊ ነውር መፈጸም ነው።

ከዚህ ኹሉ ኹኔታ የምታገኙት፡ አንድ አስተማማኝ ነገር አለ፤ ይኸም፡ እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር ኹሉ፡ መልካምና የተቀደሰ ኾኖ ሣለ፥ ይህንም፡ ራሷ፡ ሥነ ፍጥረት ጭምር የምታረጋግጠው ኾኖ ሣለ፥ ከዚህ የተነሣም፡ ይኸው እውነታ፡ "ጽድቅ"፡ ወይም፡ "እውነት" ተብሎ፡ በፍጥረተ ዓለሙ ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቶ ሊሰፍን የሚገባው፡ እርሱ ኾኖ ሣለ፥ እውን ኾኖ ያለው እውነታም፡ ይህ ኾኖ ሣለ፥ ይኼ ኹሉ ቀርቶ፡ ህልውና የሌለውና ዲያብሎስ፡ በክፋትና በርኵሰት የጠነሰሰው "ሓሰት"፡ ስሙንና መልኩን ቀይሮ፡ "ኃጢአት" ተብሎ፥ የእውነታውንም ቦታ ይዞ፡ እንዲህ መግነኑና ማየሉ፡ የሰዎች ክፉ አስተሳሰብ፡ እንዴት፡ እውነቱን፡ ሓሰት፡ ማለትም፡ ጽድቁን፡ ኃጢአት ማድረግን እንደቻለ እና እንደሚችል ነው።

## ቅዱሱ ኪዳን፡

## በምትሓታዊው የኃጢአት ቀንበር ለሚሥቃዩ፡ ያለው ምክር።

እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡራችን፡ ከፈጣሪው ቊጥጥር ሳይወጣ፡ የእርሱ መሣሪያ ኾኖ፡ የእርሱን የተቀደሰ ዓላማ ከማገልገል፡ ራሱን ሊያገልል እንደማይችል ይታወቃል፤ ለዚህ እውቅ እውነታም፡ በቀዳማዊው የሥጋ ፅንሰቱና ልደቱ፡ ወደዚህ ዓለም ያደረገው አመጣጡ፥ ቀጥሎ፡ በምድራዊ ዕድገቱና ኑሮውም ረገድ፡ በዚሁ፡ በተወለደበት ዓለም ውስጥ የሚያካኼደው ቆይታው፥ በመጨረሻው የሞት ጽዋውም፡ ከዚህ ዓለም፡ ተጠርቶ የመኼዱ ገሃድ ኹኔታ፡ በቂ ማስረጃ ነው።

እንደሰንሰለት የተያያዘው፡ ይህ ኹሉ የህልውና ኺደት፡ በዚያ ሰብአዊ ፍጡራችን ላይ በሚደርስበት ጊዜ ግን፡ በመልካሙና በክፉው፥ በእውነቱና በሓሰቱ፥ በሕይወቱና በሞቱ ረገድ፡ ያው ሰብኣዊው ፍጡራችን፡ የሚፈልገውን ለማድረግ፡ አካላዊና ባሕርያዊ ኾኖ፡ ከፈጣሪው የተለገሠው፡ ፍጹሙ የእውቀት ጸጋ፥ የመምረጡ ነጻነትና የመወሰኑ ሥልጣን፥ የማድረጉም ኃይል፡ የተጠበቀለት መኾኑ አይዘነጋም።

አኹንም፡ ያ፡ እውቅ እውነታ፡ ምንነቱ፡ ይህ መኾኑ ከተረጋገጠ፡ ታዲያ! በእግዚአብሔር በኩል የሌለውንና ያልተፈጠረውን፥ ነገር ግን፡ ክፉውን አስተሳሰብ፡ ራሱ፡ በውስጡ በማፍለቅ፥ የዲያብሎስንም መንገድ በመከተል፡ ያው ሰብአዊው ፍጡራችን፡ ለምን፡ ራሱን፡ እንዲህ፡ ለማያስፈልግ ጭንቀትና ችግር ዳረገ? ለምንስ ይዳርጋል? መልሱ፡ ቀጥተኛና አጭር ነው፡- ይኸው ሰብአዊው ፍጡራችን፡ ለዚህ ጭንቀትና ችግር የተዳረገው፡ በአፍአዊ አካሉና በውሳጣዊው ባሕርዩ በኩል፡ ከእየራሱ ሰብኣዊና ተፈጥሮአዊ፥ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ዓቅም በላይ፥ ከቊጥጥሩም ውጭ ኾነው ለሚያገኛቸው፥ ከራሱ ለሚመነጩና የራሱ ከኾኑት ኃይላት ጋር፡ ትግልንና ግጭትን በመፍጠሩ እንደኾነ፡ ግልጽ ነው።

እያንዳንዱ ሰብአዊው ፍጡራችን፥ ሴቷም ኾነች ወንዱ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ ይህንና ሌላውንም የችግር ዓይነት፡ በእየራሱ ላይ ያመጣው፡ በየጊዜያቱ፡ ተደጋግሞ እንደተብራራው፡ ፈጣሪው፡ በተፈጥሮ፡ በውስጡ ባስቀመጣቸው፡ እርሱን፡ እግዚአብሔርን በሚያስመስሉት፡ የነፍስና የሥጋ፥ የመንፈስም አካላትና ባሕርያት አማካይነት፡ የራሱ አድርጎ የሰጠውን እውቀትና በእነርሱ አማካይነት የሚነግረውን ቃል በመናቁና በመተዉ ነው፤ ንቆና ትቶም፡ ከውጭ፡ ሌሎቹ፡ የፍጥረት ተጋሪዎቹ የኾኑት መሰሎቹ ፍጡራን፥ እነርሱም፡ በሥጋ ያሉት ክፉዎች ሰዎችና በመንፈስ ያሉት ሰይጣናት የሚሉትን ብቻ፡ አውቆም ኾነ ሳያውቅ፡ በዕውርነት ስለሚከተል ነው።

ከዚህ ችግር ለመውጣት፡ ያው ሰብኣዊው ፍጡራችን፡ ይኼን የተሳሳተ አካኼዱን፡ ጨርሶ አቁሞ፡ እውነቱንና መልካሙን ወደሚያስታውቀውና ወደሚመራው፡ ወደእግዚአብሔራዊው የተፈጥሮ ምንነቱና ማንነቱ እውቀት፡ በፍጹም ንስሓ፡ መመለስ አለበት።

በዚህ ጊዜ፡ ይኸው ሰብአዊው ፍጡራችን፡ እግዚአብሔር፡ ጥንቱኑ፡ መልካምና እውን አድርጎ የፈጠረው፡ ደግነትንና እውነትን፥ ሕይወትንም እንጂ፡ መጥፎና ባዶ የኾኑትን፡ ክፋትንና "ኃጢአት" የተባለውን፡ ሓሰትን፥ ሞትንም አለመኾኑን ያውቃል።

አዎን! እነዚህን፡ የሌሉ ምትሓቶች የኾኑትን፡ ክፋትንና "ኃጢአት" የተባለውን፡ ሓሰትን፥ ሞትንም፡ በተፃራሪ አስተሳሰባቸው፡ እንዳሉ አድርገው አምጥተው፡ በሌሎች ደካሞች ሰብአውያን ፍጡሮቻችን ዘንድ፡ ተቀባይነትና ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው፥ ከዚህ የተነሣም፡ በፍጥረተ ዓለማቱ ላይ፡ እንዲህ፡ የማያቋርጥ ችግርና ሁከት እንዲደርስ ያደረጉት፡ ከመናፍስቱ መካከል፡ የመጀመሪያው ፍጡር፡ ዲያብሎስ ሲኾን፡ ከሰዎች መካከል ደግሞ፡ የመጀመሪያዋ ሴት፡ ሔዋን ናት።

ከዚያን ጊዜ አንሥቶ፡ እግዚአብሔር ያልፈጠረውና ራሱ፡ "ሓሰት" የኾነው ኃጢአት፡ ይኸው፡ እንደምናየው፡ በ"ወሊድ ቍጥጥር" ስም ሳይቀር፡ በፍጡራን ሰዎቻችን፡ የግል፥ የቤተሰብና የኅብረተሰብ ህልውናና ሕይወት ላይ፡ የቱን ያህል፡ ከባድና የተወሳሰበ የኾነ ችግርን ፈጥሮ፡ ምድራዊ ኑሯቸውን፡ እንዴት እንዳቃወሰውና በሥቃይ እንዳማሰነው፡ ይኸው ትመለከቱታላችሁ።

ስለዚህ፡ ከዚህ፡ ከሌለና ከማያስፈልግ ችግርና ሥቃይ ለመውጣት፡ እያንዳንዳችሁ ሰብአዊና ሰብአዊት ፍጡሮቻችን፡ ቆራጥ የኾነ፡ የምርጫ ውሳኔን፡ ያለአንዳች መዘግየት፡ ማድረግ ይጠበቅባችኋል። ይህም፡ እየራስን፡ የእግዚአብሔር በኾነውና በእየራስ ሰውነት ውስጥ በሚገኘው፡ የተፈጥሮ እውቀትና በእውነተኛ ንስሓ፡ ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖትና ምግባር፥ ሥርዓትና ሕይወት ማብቃት ነው።

ወደዚህ ብቅዓት የሚያደርሰው ዝክረ ነገርና መመሪያ፡ ባለፈው ኻቻምና፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፰ ዓመተ ምሕረት፡ ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በይፋ በተላለፈው፡ ቍጥር ፩/፳፻፰ ዐዋጅ እና ከእርሱ በፊት፡ "ለታላቁ ቃለ ዐዋዲ፡ ቀዳሚ መልእክት" በሚል ርእስ፡ በወጣው መግለጫ ውስጥ ይገኛልና፡ እነዚህኑ የአዋጅ መልእክቶች መመልከቱ፡ ለእያንዳንዳችሁ፡ የሚጠቅማሁ ይኾናል። ይህ ሳይኾን ቢቀር ግን፡ ሌላው ምርጫ፡ አኹን ባለው፡ የመከራና የሥቃይ ህልውናችሁ፡ በባሰ ኹኔታ መቀጠል ብቻ ይኾናል።

ከዚህ ይልቅ፡ ከላይ ባቀረብሁላችሁ የእናትነት ጥሪዬ መሠረት፡ እየራሳችሁን፡ የእግዚአብሔር በኾነውና በእየራሳችሁ ሰውነት ውስጥ በሚገኘው፡ የተፈጥሮ እውቀትና በእውነተኛ ንስሓ፡ ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖትና ምግባር፥ ሥርዓትና ሕይወት ለማብቃት ከቻላችሁ፡ በዚህ ጊዜ፡ እነዚያ፡ የፀረ እግዚአብሔር ኃይላት፡ ሳይኖሩ፡ እንዳሉ አድርገው የፈጠሯቸው፡ ክፋት፥ "ኃጢአት" የተባለው፡ ሓሰትና ሞት ተወግደው፡ በዚህ ምድራዊ ዓለም፡ በሥጋ ህልውናው ሕያው ኾኖ በሚንቀሳቀሰው፡ በዚያ ኪዳናዊ ሰውነታችሁ ውስጥ፡ የእግዚአብሔር የኾኑት፡ መልካምነትና ደግነት፥ እውነትና ሕይወት ብቻ ይሰፍናሉ።

ከዚህ በኋላ፡ "የወሊድ ቍጥጥርን" እና ከእርሱ ጋር የተያያዙትን፡ የሩካቤ ሥጋ ፍትወትን፥ የወንድን ዘርና የሴትን የወር አበባ፥ ሌሎችንም ተመሳሳይ ርእሶችን በማጠቃለል፡ ከየራሳችሁ የሰውነት አካልና ባሕርይ ጀምሮ የሚሠርፀውና የሚሰማው፥ የሚታሰበውና የሚታየው፥ የሚኾነውና የሚፈጸመው ኹሉ፡ በኃጢአት መልኩና ይዘቱ መኾኑ ቀርቶ፡ በእግዚአብሔራዊው ቅድስናና ንጽሕና ብቻ ይኾናል። ከዚያ በኋላ፡ በዚያ ኪዳናዊ፥ ወይም፡ ኪዳናዊት ሰውነት ውስጥ የሚሠርፀው አሳብና በአንደበት የሚነገረው ቃል፥ በምግባር የሚፈጸመውም፡ እንዲህ የሚል ይኾናል፡-

«እንግዴህ ወዲህ፡ ክፋትና "ኃጢአት" የተባለው ሓሰት፥ ሞትም፡ "እኔ" በምላት ነፍሴ ላይ ሥልጣን የላቸውም! በሥጋዬ፡ የእነርሱ ተገዥ ከኾንሁበት ህልውና፡ ነጻ ወጥቻለሁ! ዛሬ፡ እኔ፡ በኪዳናዊ/በኪዳናዊት ኢትዮጵያዊነቴ፡ የምኖረው ሕይወት፥ የምኾነውና የማስበው፥ የምናገረውና የማደርገው ኹሉ፡ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን ጨምሮ፡ በጋብቻ ምክንያት፡ "ጽድቅ" እንጂ፡ "ኃጢአት"፥ "ቅድስና" እንጂ፡ "ርኵሰት" አይደለም።

«ነገር ግን፡ በውስጤ ያለውና የመንፈስ ቅዱስ የኾነው ባሕርዬ፡ ማለትም፡ ኅሊናዬ፡ "ይህን ልታደርጊ አይገባም!" ብሎ፡ ለነፍሴ የሚነግራትን፡ አላደርገውም።

«ምናልባት፡ ይህንኑ፡ "ልታደርጊው አይገባም!" ተብሎ የተነገራትን ጥፋት፡ ነፍሴ፡ ከጋብቻ ውጪ የኾነ፡ የተፈጥሮ የግብረ ሥጋ ግንኙነትንም ቢኾን፡ ከዓቅሚ በላይ በኾነ፡ አንዳች ሥጋዊ ኃይልና ምክንያት ተገድዳ፥ እንዲያውም፡ አውቃም እንኳ የምታደርገው ቢኾን፡ የሥጋዬ አካልና ባሕርይ፡ በልቶና ጠጥቶ፡ እንደመጸዳዳቱ የተፈጥሮ ግዳጅ እንደተካኼደ ቈጥሬ፡ እፈጽመው ይኾናል እንጂ፡ "ኃጢአት" መኾኑን አምኜ አላደርገውም፤ አለዚያ፡ ገና፡ የኃጢአት ቀንበር ተሸካሚ መኾኔን ማመን ይኾንብኛልና።

«እውነታው ግን፡ ኃጢአት፡ በእኔ ላይ ሥልጣን ስለሌለው፥ እርሱዉም፡ ከእግዚአብሔር አብ እና ከእግዚአብሔር እም፡ ከድንግል ማርያም በተወለደው፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሢሕ ቤዛነት ባገኘሁት ንስሓዬ፥ ቀደም ብሎም፡ **"ወነአምን በአሓቲ ጥምቀት፡ ለስርየተ ኃጢአት!"፡ "ኃጢአት በሚሰረይባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን!"** በምትለው ሃይማኖቴ፡ ለአንዴና ለዘለዓለም ስለተሰረየልኝ፡ ከኃጢአት ነጻ በኾነው፡ በዚያው የቅድስናና የንጽሕና ሕይወቴ እቀጥላለሁ እንጂ፡ ባለማወቅ፡ የእርሱ ተገዢ ኾኜ ስሠቃይ ወደቆየሁበት የባርነት ኑሮዬ፡ ፈጽሞ አልመለስም።

«በሰውነቴ የተፈጥሮ አካላትና ባሕርያት ግፊት፡ ምናልባት፡ አኹንም፡ ከዓቅሜ በላይ በኾነ ኃይልና ምክንያት፡ ተገድጄም ኾነ አውቄ፡ የፈጸምሁት ያ፡ የቀደመው የጥፋት ድርጊቴ ቢደጋገምም፡ አኹንም፡ ራሴን፡ ከዚያ፡ የቅድስናና የንጽሕና ሕይወቴ ላለማውጣትና ተመልሼ የኃጢአት ቀንበር ተሸካሚ ላለመኾን፡ በዚያው መጠን፡ በሚደጋገመው ንስሓዬ አማካይነት፡ ራሴን እያጸዳሁ እቀጥላለሁ እንጂ፡ በምንም ኹኔታ፡ በኃጢአት ኃይል ተሸንፌ፡ ራሴን፡ ለክፋትና ለሞት አሳልፌ፡ ከቶ አልሰጥም።

«አዎን! "እግዚኦ! ሚመጠነ፡ እመ አበሰ ሊተ እኁየ፡ እኅድግ ሎቱ? እስከ ስብዕኑ?" ፡ "ወንድሜ፡ ቢበድለኝ፡ ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው? ሰባት ጊዜን?" ብሎ፡ ሓዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ላቀረበለት ጥያቄ፡ "ኢይብለከ፡ 'እስከስብዕ፤ አላ፡ እስከሰብዓ፡ በበስብዕ።'" ፡ "የለም! 'እስከሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ፡ እስከሰባት ብቻ አልልህም!'" ሲል፡ አምላኬ መድኃኒቴ ኢየሱስ መሢሕ በሰጠው የተትረፈረፈ የምሕረት ቸርነቱ ተጠቅሜ፡ መልካሙን ኪዳናዊ ሕይወቴን፡ በቅዱሱ ኪዳን የተዋሕዶ ሃይማኖታዊው እና ምግባራዊው ንስሓዬ አንጽቼ፥ በጽድቅና በንጽሕና ነጻነቴም አጽንቼ እቀጥላለሁ።» (ማቴ. ፲፰፥ ፳፩-፳፪።)

እንግዴህ፡ ይኼ ነው፡ በዚህ፡ በተነሣንበት ርእሰ ጉዳይ ረገድ ያለው፡ የአንድ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ እና የአንዲት የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊት ልጆቼ እውነተኛነትና ታማኝነት፥ ቆራጥነትና ጀግንነት ተለይቶ የሚታወቀውና ጠርቶ የሚገለጥበት ሃይማኖታዊ የሕይወት ዛፍነትና ምግባራዊ የንስሓ ፍሬ።

ስለዚህ፡ ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሢሕ፡ ለዚሁ ብሎ፡ ከእኔና በእኔ፡ ሰው ኾኖ ተወልዶ፥ በመስቀልም ላይ፡ ቅዱስ ሥጋውን በመቍረስ፥ ክቡር ደሙንም በማፍሰስ፡ ይህን በሚያህልና ይህን በሚመስል መሥዋዕትነት ባስወገደው፡ "ኃጢአት" በተባለው የሌለ "ጉድ፥ ጭራቅ" ቀንበር ሥር ወድቃችሁ፡ በእርሱ ጠንቅ የምትማቅቁ ልጆቼ ኹሉ አይዟችሁ! በዚህ፡ በኪዳነ ምሕረታችን፡ የምሥራቹ ቃሌ፡ ደስ ብሏችሁ፡ ተጠናከሩ! በሌለው የኃጢአት ጦር፡ የቱንም ያህል ተወግታችሁና ተሸንፋችሁ የቆሰላችሁ መስሎ ቢታያችሁ፡ ኹልጊዜም፡ በንስሓ፡ እንደገና፡ ፍጹም ጤና መኾንና ከወደቁበት መነሣት አለና፡ "ኃጢአት" ከተባለው ሓሳዊ ቀንበር፡ እየራሳችሁን፡ ፈጽማችሁ ነጻ አውጡ!

ኃጢአት፡ የለም እንጂ፡ እናንተ፡ "አለ!" ካላችሁ፡ እርሱ ይፍራችሁ፥ ይሽሻችሁ እንጂ፡ እናንተ አትፍሩት! ደፍሮ፡ በሓሳዊ ምትሓትነቱ፡ ወደእናንተ እንደመጣባችሁ ካሰባችሁም፡ በእግዚአብሔር መልካምነትና እውነት፥ ቅድስናና ንጽሕና በሚያምነው መንፈሳችሁ ኾናችሁ፡ "በእኔ ዘንድ ያለው፡ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንጂ፡ አንተ አይደለህም። አንተማ የለህም። ስለዚህ፡ አንተ ሰይጣን! ከፊቴም፥ ከኋላዬም ወግድ!" ብላችሁ፡ በአሸናፊነት ተጋፈጡት! ተቋቋሙት! አስወግዱትም!

ከዚህ በኋላ፡ በዚህ መንፈስ ቅዱሳዊ አቋም ኾናችሁ፡ ያን፡ እርሱ፡ በኃጢኣትነት የመጣበትን ግብር፡ ከዓቅማችሁ በላይ በኾነ፡ በተፈጥሮአዊው ፍትወተ ሥጋችሁ ተገፋፍታችሁ ብትፈጽሙት እንኳ፡ ይህ፡ ግዳጅ፡ መልካሙ የእግዚአብሔር ዕቅድ ሊፈጸምበት የመጣ፡ "ጽድቅ እና ቅድስና ነው!" ብላችሁ ተቀበሉት እንጂ፡ "ኃጢኣትና ርኵሰት ነው!" አትበሉት። ምናልባት ግን፡ በዚህ ድርጊታችሁ፡ ጥፋተኝነትና በደለኛነት ቢሰማችሁ እንኳ፡ ወዲያው፥ እዚያው፡ በእውነተኛ ንስሓችሁ አስወግዱት።

የእግዚአብሔር እውነት፡ በዚህ ረገድ፡ በእኔ አንደበት፡ ለእናንተ እየተናገረች ያለችው፡ ይኼ የአዋጅ ቃል፡ ስለኃጢኣት ብቻ ሳይኾን፡ ስለግብረ አበሮቹ፡ ስለክፋትና ስለሞትም ጭምር ስለኾነ፡ ያ፡ የእግዚአብሔር የእውነት ቃል፡ በእነዚህም ላይ የጸናና የሚጸና መኾኑን፡ ልታውቁት ይገባችኋል።

## ቅዱሱ ኪዳን፡
## ስለጋብቻና ስለሩካቤ ሥጋ፡ ለትውልዱ የሚለው።

በዚህ ረገድ፡ በተለይ፡ አኹን የተነሣንበትን፡ "የወሊድ ቊጥጥርን" በሚመለከት፡ በተለይ፡ የዘመኑ ሰብአዊ ትውልዴ፡ ለምን፡ ወደዚህ፡ ወደማያስፈልግ ችግር ውስጥ እንደተዘፈቀ ላመልክታችሁ!

በመጀመሪያ ነገር፡ ኹለቱም ጾታዎች፥ ወይም፡ አንዳቸው፡ የሩካቤ ሥጋ ፍትወታቸውን ተቆጣጥረው መግታት የማይችሉ ከኾኑ፡ ይህንኑ ፍትወት፡ በመልካምነትና ለመልካሙ ሕያው ዓላማ የፈጠረው ፈጣሪ፡ ለዚህ ችግር፡ ቀላልና ተገቢ የኾነውንም፡ መልካም መፍትሔ፡ ዐብሮ ፈጥሮ፡ የአፈጻጸሙን ሥርዓት ጭምር፡ አደላድሎ የሠራ መኾኑን ማወቅ ነው። ያም የመፍትሔ ሥርዓት፡ <u>ጋብቻ</u> ነው።

ጋብቻን ላለመፈጸም፡ በተለይ፡ በዛሬው ዘመን፡ የሚቀርቡ፡ ሥፍር ቊጥር የሌላቸው ምክንያቶችና ሰበቦች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን፡ እነዚህ ምክንያቶችና ሰበቦች፡ የቱንም ያህል በርካታና ከባዶች መስለው ቢታዩም፡ ጋብቻ በተቀመጠበት፡ በሌላው የሚዛኑ ቊና ላይ ሠፍረው፡ የእግዚአብሔር ሥርዓት የኾነውን፡ እርሱን፡ ጋብቻን፡ በክብደታቸው ሊደፉት፡ ከቶ አይቻላቸውም። መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "**ይቀልል፡ ሰማይ ወምድር ይኅልፍ፡ እምትደቅ፡ አሓቲ ቃል፡ እምኦሪት፥ ወእምነቢያት።" ፡ "ከሕግና ከትንቢት፡ አንዲት ቃል ከምትወድቅ፡ ሰማይና ምድር ቢያልፍ ይቀላል።"** ያለው መለኮታዊ ቃል፡ እዚህ ላይ የሚጸና መኾኑን ማስተዋል ይገባችኋል። (ሉቃ. ፲፮፥ ፲፯።)

ጋብቻ፡ "አያስፈልገኝም!" በማለት፡ ለመነኵሳቱም እንኳ ያልተቻለውን፡ ከዚሁ፡ ከጋብቻ፡ ጨርሶ ለመገለል ቀርቶ፤ ተፈጥሮአዊ ምልክቱ የኾነው፡ የፍላጎቱ ዕድሜ ከሚጠይቀው በላይ፡ እርሱን፡ ጋብቻን ለማዘግየት መሞከሩ እንኳ፡ ማናችሁንም፡ ከዚህ መለኮታዊ የማስጠንቀቂያ ቃል፡ ነጻ አያደርጋችሁም።

"አታመንዝር" የሚለውን፡ ከዐሥሩ የእግዚአብሔር ቃላት፡ አንዱ የኾነውን፡ ሃይማኖታዊ ምግባር፡ አክብራችሁ ለመጠበቅና ለመፈጸም፡ በጋብቻ መወሰን ያስፈልጋችኋል፤ ይገባችኋልም፤ ሌላ ማማረጫ የለም። ይህ የእግዚአብሔር እውነታ፡ በተፈጥሮ ጸጋ፥ ወይም፡ በመንፈስ ቅዱስ ጥሪ፡ የሠመረ ኾኖ፡ በኢትዮጵያዊው የድንግልናና የብሕትውና ሥርዓት ከሚፈጸመው በቀር፡ በባዕዳኑ የምንኵስና ቀንበርም እንኳ ቢኾን ሊሻር አልተቻለም፤ አይቻልምም። (ማቴ. ፲፱፥ ፲-፲፪።)

እዚህ ላይ፡ ከዐሥሩ የእግዚአብሔር ቃላት መካከል፡ አንዱ የኾነው፡ "አታመንዝር!" የሚለው ርእሰ-አንቀጽ፡ ያለጋብቻና ከጋብቻ ውጪ ከሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ጋር አግባብነት ስላለው፡ በዚህ ረገድ፡ የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ፡ ምን እንደሚል፡ በእኔ ቃል፡ እስኪ፡ ጥቂት ላስረዳችሁ!

"አመንዝራነት"፡ ወረተኛነት፥ ይኸውም፡ በአንድ ጸንቶ አለመርጋት መኾኑን ታውቃላችሁ። ለዝሙት ብቻ ሳይኾን፡ ለሌሎች ግብሮች፥ በተለይና በይበልጥ፡ ለአምልኮም ይውላል። አንዱን ፈጣሪ እግዚአብሔርን ማምለክን ትቶ፡ ሌላ፡ ጣዖትን፥ ያም፡ ሕያዋን ፍጡራን የኾኑትን መናፍስትንና ሰዎችን፥ በድን የኾነ ቅርፅን ብቻ ሳይኾን፡ ገንዘብን ጨምሮ፡ ሥጋዊ የኾነውን፡ ሀብትን፥ እውቀትንና ሥልጣንን፡ "አምላክ" አድርጎ፡ ለዚያ መስገድ ወይም መገዛት፡ አመንዝራነት ነው።

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ፡ "የእግዚአብሔር ሥርዓት ነው!" ብላችሁ አምናችሁበት እየፈጸማችሁት የኖራችሁትና የምትኖሩት ጋብቻ፡ እንደአዳምና ሔዋን፡ በእግዚአብሔር መንግሥት፡ እስከሞትና ከዚያ በኋላ በሚጸና አንድነት፡ ህልውናን፡ በሕያውነት መቀጠል ነው።

በዚህ አንጻር፡ በተቃራኒነት ያለው አመንዝራነት ግን፡ ይህን፡ እግዚአብሔራዊ ሥርዓት ትቶ፡ የተቀደሰውን ጋብቻ፡ ኹለቱም ባልና ሚስት፥ ወይም አንዳቸው፡ በፈለጉ ጊዜ፡ እያፈረሱትና፡ እየለዋወጡት፥ እነርሱም፡ እየተፋቱና ከሌላው ጋር፡ ሌላ ሰውኛ ጋብቻን፡ እንደገና እየመሠረቱ፡ ባለመጽናትና በወረት መኖር ነው። "የእሥራኤል ልጆች ነን!" የሚሉት አይሁድና የእስማኤል ልጆች የኾኑት እስላሞች፥ አረማውያንና አሕዛብም እንደሚያደርጉት።

በተለይ አይሁድ፡ "ለምንት አዘዘ ሙሴ፡ የሀቡ መጽሐፈ ፍልጣን፤ ወይኅድግዋ!"

"ባል፡ የፍቺዋን ሰነድ ሰጥቶ፡ ሚስቱን እንዲያሰናብታት፡ ታዲያ! ለምን ሙሴ አዘዘ?" ብለው፡ ልጄ ወዳጄን፡ ኢየሱስ መሢሕን በጠየቁት ጊዜ፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓት ያፈረሰው፡ ይኸው፡ የአይሁድ ኦሪታዊ የጋብቻ ሕጋቸው፡ ብልሹ መኾኑን፡ በግልጽ በማስታወቅ፡ የሰጣቸውን ምላሽ ታስታውሱታላችሁ።

ይኸውም፡ "ሙሴስ አዘዘክሙ፡ በከመ እከየ ልብክሙ፡ ትኅድጉ አንስትያክሙ፤ ወበቀዳሚ ፍጥረትሰ፡ አኮ ከማሁ።"

"ሙሴማ፡ ከልባችሁ ክፋት የተነሣ፡ ቢቸግረው፡ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ፡ ባይኾን፡ ሚስቶቻችሁን፡ በጽሑፍ የፍቺ ሰነድ እንድታሰናብቱ ፈቀደላችሁ።

"በፍጥረት መጀመሪያ ግን፡ እንዲህ አልነበረም። ሙሴም፡ «እግዚአብሔር፡ በጋብቻ፡ መልሶ ያጣመረውን፡ የባል እና ሚስት አንድነት፡ እንግዴህ፡ ሰው አይለየው!» በሚል ዘለዓለማዊ ቃል፡ የፈጣሪ ሥርዓት ኾኖ፡ ለአዳም እና ለሔዋን የተሰጠውን ትእዛዝ አላፈረሰም። ያፈረሳችሁ፡ እናንተ ናችሁ!" የሚለው ቃሉ ነው።

ልጁ ወዳጁ፡ ይህን ብሎ፡ ዐመፃቸውን ከነቀፈባቸው በኋላ፡ "አመንዝራነት"፡ ጋብቻን፡ ኾነ ብሎ ለማፍረስ በታቀደ ዓላማ፡ ዝሙትን መፈጸም እንጂ፡ በንስሓ ሊጸዳ በሚችል የአጋጣሚ ድክመት፡ መወዳደቅንና ሌሎችን ጥቃቅን የስሕተት ምክንያቶችን የሚያጠቃልል አለመኾኑን፡ እንዲህ በሚለው፡ መለኮታዊ ቃሉ አረጋግጧል፡-

"እብለክሙ አነሂ፡- «ኵሉ ዘይኀድር ብእሲቶ፡ ዘእንበለ ትዘሙ በላዕሌሁ፡ ለሊሁ፡ ረሰያ ዘማ፤ ወእንተሂ ደኀርዋ አውሰበ፡ ዘመወ።" ፡ "ያለዝሙት ምክንያት፡ ሚስቱን ፈትቶ፡ ሌላዪቱን የሚያገባ ኹሉ፡ ያመነዝራል፤ የተፈታችውንም የሚያገባ፡ ያመነዝራል።" (ማቴ. ፲፱፥ ፫-፲፫።)

ስለዚህ፡ ጋብቻን አጽንተው እያሉ፡ ከጋብቻ ውጪ፡ ከሌላ ጾታ ጋር የሚደረግ ሩካቤ ሥጋ፡ በንስሓ የሚነጻ የዝሙት ኃጢአት ሲኾን፡ ራሱን ጋብቻን ማፍረስ ግን፡ "አታመንዝር!" ያለውን፡ ከአሥሩ፡ የእግዚአብሔር ቋሚ ቃላት፡ አንዱ የኾነውን፡ መተላለፍ፥ ወይም፡ ማፍረስ እንደኾነ፡ ከላይ የተጠቀሰው፡ የልጁ የወዳጁ ቃል፡ በሚበቃ ያስረዳችኋል።

እናንተ ልጆቼ ግን፡ አይዟችሁ! ከልዑል እግዚአብሔር አብ እና ከእኔ ከእግዚአብሔር እም፡ ቀድሞ፡ ከፍጥረት በፊት፡ በመለኮትነት፥ ኋላም፡ በመጨረሻው የሕይወት ዘመን፡ በሰውነት ተወልዶ፡ ለዚህ ኹሉ፡ የልጆቻችንና የፍጡሮቻችን በደል፡ ቤዛ በኾነው ልጃችን፡ በኢየሱስ መሲሕ የመስቀል መሥዋዕትነት፡ እነዚህ፡ የዝሙትና የአመንዝራነት "ኃጢአቶች"፡ በንስሓችሁ የሚነጹና የሚስተካከሉ ኾነዋልና፡ ደስ ይበላችሁ!

እግዚአብሔር፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ብሎ፡ በመልኩ የፈጠረውን ሰው እንዲያስገኝለት የሠራውን፡ ጋብቻንና ሥርዓቱን፡ ሕያውና ጤናማ አድርጎ ለማቆየት፡ ይኸው የጋብቻ ሥርዓት፡ በራሱ የሚፈጽማቸውን ትንግርቶች መመልከት ነው፤ ከእነዚህ መካከል፡ አግባብነት ያላቸውን፡ አንዳንዶቹን፡ የምታውቋቸውን፡ እዚህ ላይ ላውሳላችሁ!

እነርሱም፡ <u>የጋብቻ የተፈጥሮ ፍላጎት፡</u> በሰብአውያን ፍጡሮቻችን፥ በወንዶቹም፥ በሴቶቹም ልጆቻችን ዘንድ አለመቀነሱ፡ አንዱ ትንግርት ሲኾን፥ በእርሱ አማካይነት፡ **<u>የሚፀነሱትና የሚወለዱት፡ የወንዶችና የሴቶች ልጆቻችን ብዛት፡ ምንጊዜም ተመጣጣኝ ኹኖ መቀጠሉ፡</u>** ሌላው ትንግርት ነው።

በጋብቻ የቃል ኪዳን ሥርዓት የምትኖሩ ባለትዳሮች ልጆቻችን፡ ለዚህ፡ እናንተው፡ "ችግር" ላላችሁት፡ እግዚአብሔራዊ ጸጋ፥ ወይም፡ የተፈጥሮ በረከት፡ ሃይማኖታዊ የኾነውን መፍትሔ ለማግኘት፡ በዚህ መልክና ይዘት፡ እናንተው ባልና ሚስቱ፡ ለእኔ ለእናቱና ለአባቱ ለእግዚአብሔር አብ፥ ለእርሱም፡ ለልጃችን ለኢየሱስ መሢሕ፡ የባሕርይ ሕይወት የኾነውን፡ መንፈስ ቅዱስን በመካከላችሁ፡ ሦስተኛ አባል አድርጋችሁ፥ እርሱ የሚሰጣችሁን መመሪያ ተከትላችሁ፡ ኹለታችሁም ባለትዳሮች፡ በስምምነት የምትመካከሩበትና የምትወስኑት እንጂ፡ "የወሊድ ቍጥጥር" በተባለው ክፉ ወጥመድ ውስጥ፡ በቀጥታ ገብታችሁ፡ እየራሳችሁን ሊታጠላልፉ የሚያስፈልጋችሁ አይደለም።

ምናልባት፡ ከዚህ ውጭ የምታደርጉት፡ ሌላ፡ የግል ነገር ቢኖራችሁ፡ ያ ነገር፡ ከኹለታችሁ፡ በአንዳችሁ፥ ወይም፡ በኹለታችሁም ላይ፡ እየራሳችሁ ከፈጸማችሁት ጥፋት የተነሣ፡ የጤንነት ጒድለትንና የሕይወት ማጣትን ጠንቅ የሚያስከትልባችሁ ኾኖ፡ በእምነታችሁ ድክመት ምክንያት፡ የምትሰጡት፡ የተለየ ውሳኔ ሊኾን ይችላል።

ለዚህ፡ ለእምነታችሁ ድክመት፡ ጠንቅ የኾነውን ምክንያትና መፍትሔውን ደግሞ፡ እንደሚከተለው ቀርብላችኋለሁ! በመጀመሪያ ነገር፡ እናንተ ኹለት ባለትዳሮች ልጆቻችን፡ በሃይማኖታችሁና በምግባራችሁ፥ በኑሮ ሥርዓታችሁና በሕይወታችሁ፡ በቅድሚያ፡ እየራሳችሁን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ያበቃችሁ፥ ጋብቻችሁንም፡ በዚሁ መሠረት የፈጸማችሁ፥ ወይም፡ ያስተካከላችሁ መኾን ይኖርባችኋል።

ከዚህ በኋላ፡ የእናንተ፡ የባለትዳሮቹ ልጆቻችን የመጨረሻ ዕድል፡ **ያለአንዳች ጭንቀትና ሥጋት፥ ያለምንም ችግርና ሁከት፡ በፍጹሟ የእግዚአብሔር ነጻነትና ፍቅር፥ ደስታና ሰላም፡ ዘለዓለማዊቷን፡ የትንሣኤና የሰንበት ሕይወት፡ በፍጹሟ፡ የነፍስ፥ የሥጋና የመንፈስ ዕረፍት መኖር ብቻ ነው።**

በዚህ መልክ በተከናወነው፡ የተቀደሰ ጋብቻችሁ፡ ይህን በመሰለው ሕይወት እየኖራችሁ ያላችሁት፡ እናንተ ኪዳናዊው ባል እና ኪዳናዊቷ ሚስት ልጆቻችን፡ መኻታችሁ፡ የተቀደሰ ኾኖ፡ በማናቸውም ጊዜ፡ ተስማምታችሁና ተፈቃቅዳችሁ በምትፈጽሙት ሩካቤ ሥጋችሁ፡ በፍጹም ተደስታችሁ፡ ይህን ኹሉ መልካም ስጦታን ላበረከተላችሁ፡ ለቸሩ ፈጣሪያችሁ፡ የማያቋርጥ ምስጋናችሁን በማበርከት፡ የትዳር ህልውናችሁን፡ እየተዝናናችሁ ትቀጥላላችሁ።

እናንተ፡ የቃል ኪዳን ባለትዳሮች ልጆቻችን፡ መልካሙን ሕይወታችሁን፡ እንዲህ በምትኖሩበት ጊዜ፡ ይህንኑ፡ መልካሙን ኑሮአችሁን፡ በእግዚአብሔር ምስጋናና በሰብአዊ እርካታ ከመቀጠል በቀር፡ ልጆችን ስለመውለድ፥ እነርሱም፡ ወንዶች፥ ወይም፡ ሴቶች ስለመኾናቸው፥ ስንት መኾን እንዳለባቸውም፥ እነርሱንም፡ መቼ፥ መፅነስና መውለድ እንዳለባችሁ፥ እነዚህንና እነዚህን ስለመሰሉት የተያያዙ ጉዳዮች፡ የምታስቡትና የምታቅዱት፥ የምትሠጉበትና የምትጨነቁበትም፡ አንዳችም ነገር ሊኖር ከቶ አይገባም።

ይኼማ፡ የእናንተ ጉዳይ ሳይኾን፡ የእኔ፡ የእናታችሁ እና የቃል ኪዳን አባት አምላካችሁ፡ መለኮታዊ ሥልጣንና የኃላፊነት ድርሻ ነው፤ ይህንም እውነታ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ አማካይነት ያገኛችሁት፥ ያመናችሁበትና የምትኖሩበት፡ እግዚአብሔራዊው እውቀት፡ በትክክልና በአጽንዖት አረጋግጦ አስገንዝቧችኋል። በዚህ እግዚአብሔራዊ እውቀታችሁ መሠረት፡ እናንተ፡ ኪዳናዊው ባልና ኪዳናዊቷ ሚስት ልጆቻችን፡ የቱንም ያህል የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ብታደርጉ፡ ከወንድ አብራክ ወጥቶ፡ በሴት ማሕፀን የሚያርፈውን፡ የተባዕቱን ዘር፡ በመለኮታዊ ፈቃዱና ጥበቡ፡ በእንስቲቱ ወርኃዊ ደም አማካይነት፡ በእግዚአብሔር መልክና "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" ለተባለው ለሰውነት ፅንስና ሽልነት የሚያበቃው፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብቻ መኾኑን፡ አበክራችሁ ታውቃላችሁ።

በዚህ ዓይነት፡ እልፍ አእላፋቱን ከያዘው፡ ከወንዱ አብራክ የዘር ቋት መካከል፡ እርሱ፡ እግዚአብሔር ብቻ በሚያውቀው ምሥጢራዊ ጥበቡ፡ ከእርሱ፡ ከእግዚአብሔር ተከፍላ፡ በዚያ ማሕፀን ውስጥ ከምትገኘው፡ ከነባቢቷ፥ ለባዊቷና ሕያውቷ ነፍስ ጋር፡ በሴቲቱ ማሕፀን ውስጥ፡ ከደሚ ጋር ተዋሕዶ፡ ለዚያ፡ የሰውነት ፍሬ የሚበቃው፡ የትኛው፡ አንዱ፥ ወይም፡ ኹለቱ፥ ወይም፡ ከዚያም በላይ፡ ስንቱ ዘር እንደኾነ፥ ያም፡ በጾታው፡ ወንድ፥ ወይም፤ ሴት እንዲኾን የሚያደርገው፥ ፅንሱም፡ መቼ ሊኾን እንደሚገባው፡ የሚያውቀውና የሚወስነው፥ ያው፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው።

በአጠቃላይ፡ በምድር ላይ፡ ሰውን ጨምሮ፡ ምን ያህል የፍጥረት ወገን ሊኖር እንደሚገባ፡ መጥኖ ማስተካከል የሚቻለው፥ ለዚህም ኹሉ ክዋኔ፡ ከውጥኑ አንሥቶ፡ እስከፍጻሜው፡ መብቱና ችሎታው፥ ሥልጣኑና ኃይሉ ያለው፡ እርሱ፡ የፍጥረተ ዓለማቱ ፈጣሪና ባለቤት የኾነው፡ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

እናንተ፡ ባልና ሚስቱ ልጆቻችን፡ በተፈጥሮ ሥርዓታቱ፡ መንፈሳዊውን ቅድስናና ሥጋዊውን ንጽሕና፡ ጠብቃችሁና ተከትላችሁ ከምትፈጽሙት በቀር፡ አዎን! በዚህ ክንውን ውስጥ፡ ከውጥኑ አንሥቶ፡ እስከፍጻሜው ድረስ፡ እናንተን የሚያገባችሁ፡ አንዳችም ተሳታፊነት፡ ፈጽሞ የለም።

በዚህ ረገድ፡ ለእናንተ የሚኾናችሁን፥ የሚያስፈልጋችሁንና የሚገባችሁን፡ የቸርነቱን ሥራ የሚያደርግ፥ የሚያካኺድና አከናውኖ የሚፈጽም፥ ለፍሬም የሚያበቃ፡ ከእኔ ከመርዓቱና ከልጃችን፡ ከኢየሱስ መሢሕ፥ ከመንፈስ ቅዱስም ጋር፡ እርሱ እግዚአብሔር አብ መኾኑን፡ እናንተም ታውቃላችሁ።

ይኹን እንጂ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ በኹሉም አግጣጫ እንደሚታየው፡ ሰዎች፡ የእግዚአብሔርን ትተው፡ የራሳቸውን ስሑት (የሓሰት) መንገድ በሚከተሉበት ጊዜ፡ የሚደርሰው ኹናቴ፡ ይኸው ዛሬ፡ ከእውነተኛዪቱ ሃይማኖት ከመራቅ የተነሣ፡ "የወሊድ ቍጥጥርን"፥ በእርሱም ጠንቅ፡ በሰዎች ላይ እየደረሰ ያለውን፡ ጽኑና ቀሣፊ፥ ታላላቅና የተለያዩ የኾኑ ችግሮችን፡ በራስ ላይ እንዲደርስ መጋበዝ መኾኑን፡ እነሆ፡ ሰብአዊው ፍጡራችን ኹሉ፡ በገሃድ የሚመለከተው ነው።

የእናንተ፡ የባልና ሚስቱ ልጆቻችን ድርሻ፡ የአባታችሁ፡ የልዑል እግዚአብሔር አብ እና የእኔ የእግዚአብሔር እም እናታችሁ ልጆች የመኾናችሁን ጸጋ ለመቀበል፥ በባሕርይ ልጃችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ክህነታዊ ንጉሥነትና በእኔ፡ በእናቱ አገራዊ ንግሥትነት በምትመራው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ ባለሙሉ መብት፡ ዜጎች ብቻ ሳትኾኑ፡ ነጋሢዎችም የመኾናችሁን ክብር ለመቀዳጀት፥ በመጨረሻም፡ ይህችኑ፡ መለኮታዊት መንግሥትና እኛን መሪዎቿን የምታገለግሉ ካህናት የመኾናችሁን ሢመት ለመጐናጸፍ የበቃችሁባትን፡ የቅዱሱ ኪዳን፡ ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁንና ምግባራዊ ሥርዓታችሁን፡ በፍጹም ታማኝነት ጠብቃችሁና ፈጽማችሁ መኖር መኾኑን፡ እናንተ፡ ኹለታችሁም ባለትዳሮች ልጆቻችን ታውቃላችሁ።

በእናንተ በኩል ይህን ድርሻችሁን አውቃችሁና ጠንቅቃችሁ ከፈጸማችሁ፡ ሰውኛው "የወሊድ ቍጥጥር"፡ "ሊያደርግ ይችላል!" ተብሎ የሚታሰበውን ብቻ ሳይኾን፡ ከማይታሰበውም በላይ፡ ለእናንተ፡ ምድራዊና ዘለዓለማዊ ሕይወት፡ የሚበጃችሁንና የሚጠቅማችሁን፡ ነፍሳዊና ሥጋዊ፥ መንፈሳዊም ትንግርት፡ በቅዱሱ ኪዳን ያመናችሁበትና የተማመናችሁበት፡ ቸሩ አባታችሁ፥ እኔም እናታችሁ፡ ፈጽመንላችሁ ታገኙታላችሁ።

## ቅዱሱ ኪዳን፡
## ስለጋብቻ መሠረታዊ ዓላማ የሚለው።

በሥነ ፍጥረት ሥርዓት፡ በወንድ እና በሴትነት ጾታ ተለይቶ የተከሠተው፡ እግዚአብሔራዊው የጋብቻ ዓላማ፡ መሠረታዊ ግቡ፡ "መውለድ"፥ "መዋለድ" መኾኑን፡ በኦሪት ዘፍጥረት፡ ምዕራፍ ፩፥ ቍጥር ከ፳፯ እስከ፳፰ ላይ ተጽፎ የሚነበበው፡ **"ብዝኁ! ወተባዝኁ! ወምልዕዋ ለምድር።" : "ብዙ! ተባዙ! ምድርንም ሙሏት!"** የሚለው ቃል፡ አረጋግጦ ያመለክታችኋል።

በዚህ ረገድ፡ ከእናንተ በፊት የነበሩት፡ "የእግዚአብሔር ልጆች"፥ "የኢትዮጵያ ልጆች" የተባሉት፥ ዛሬም፡ በዚሁ ስም የምትጠሩት፡ እናንተ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያት እና ኢትዮጵያውያን ልጆቻችን፡ ለዝንተ ዓለም፥ ይህም እንግዴህ፡ ለ፯ሺ፭፻፺ ዓመታት መኾኑ ነው፤ ጠብቃችሁትና አክብራችሁት፥ ተከትላችሁትና አጽንታችሁት ስትፈጽሙት የኖራችሁት፥ ዛሬም፡ እየፈጸማችሁ ልትኖሩት የሚገባችሁ፡ የባልና ሚስት የጋብቻና የመኻታ፡ እርሱም፡ የሩካቤ ሥጋ ሥርዓትና ዝክረ ነገር፡ ይህን የሚመስል እንደኾነ፡ እስካኹን የተናገርሁት ቃሌ፡ በሚበቃ ያስረዳችኋል።

እርሱንም፡ ልብ አድርጋችሁ ታስተውሉትና ታስቡት ዘንድ፡ እዚህ ላይ፡ እንደገና አጠናክሬና በአጭር ቃል አጠቃልዬ አቀርብላችኋለሁ፡-

> እግዚአብሔር፡ በአዳም እና በሔዋን የመሠረተውና የጀመረው፥ እስከዛሬና አኹን፥ ወደፊትም እየኾነና እየተፈጸመ የሚቀጥለው፡ እውነተኛውና የሚጸናው ጋብቻ፡ ይህ ነው፡- እርሱ እግዚአብሔር ብቻውን ባወቀ፥ እናንተ፡ ወንድዬውና ሴቲቱ ልጆቻችን ግን፡ በማታውቁት፥ ልታውቁትም በማይቻላችሁ መንገድ ተገናኝታችሁ ትተዋወቃላችሁ፤ በዚህ መተዋወቃችሁ አማካይነት፡ በእግዚአብሔር ስም፡ በፍጹም ፍቅርና ስምምነት ከተዋደዳችሁ፥ በመንፈስ ቅዱስ ሽምግልናና እማኝነት፡ ለጋብቻ ባልና ሚስትነት ትፈቃቀዳላችሁ።
>
> እንዲህ፡ በእውነት ከተፈቃቀዳችሁ፡ ቃል ኪዳናችሁን፡ ለብቻችሁ ታደርጋላችሁ። ከጥሩት ውኃ በኋላ፡ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊው ልጃችን፥ ካህናችንና ነጋሢያችን በኾነው፡ በመልከ ጼዴቅ ኀብስተ አኰቴትና ጽዋዓ በረከት መሥርተን፡ በፍጻሜው የሕይወት ዘመን፡ በልጁ በወዳጁ፡ በኢየሱስ መሢሕ፡ የምሕረት ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ዘለዓለማዊ ያደረግነውን ሥርዓት ቍርባን፡ ዐብራችሁ በመቀበል፡ ያን የጋብቻ ቃል ኪዳናችሁን፡ ታጸኑታላችሁ፤ ታጸድቁታላችሁ፤ ታትሙታላችሁ፤ ትቀድሱታላችሁም።
>
> በዚህ ጊዜ፡ <u>በቃ! እግዚአብሔር፡ በአዳም እና በሔዋን የመሠረተውና የጀመረው፥ እስከዛሬም የቀጠለው፥ ለወደፊትም፡ በሕያውነት የሚኖረው፡ እውነተኛው ጋብቻ ተፈጸመ፤ የጸናም ኾነ! አለቀ!</u> በዚህ ጊዜ፡ በብሉይ ኪዳኑ የተነገረውና በአዲስ ኪዳኑ የጸደቀው፡ እንዲህ የሚለው የእግዚአብሔር ቃል፡ እውን ይኾናል፡- "**ዘፈጠሮሙ እግዚአብሔር እምትካት፡ ተባዕተ፥ ወአንስተ ገብሮሙ፤ ...እንከሰኬ፡ ኢኮኑ ክልኤተ፤ አላ አሐዱ ሥጋ እሙንቱ፤ ዘእግዚአብሔር አስተፃመረ፡ ሰብእ ኢይፍልጥ።**"
>
> "**በመጀመሪያ፡ እግዚአብሔር፡ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፤ ...እንግዴህ፡ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ፡ ኹለት አይደሉም። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አንድ ያደረገውን፡ ሰው አይለየው!**"

ይህ ነው፡ የእግዚአብሔር የጋብቻ ሥርዓት። ይህ፡ የእግዚአብሔር ሥርዓት፡ በመንፈስ ቅዱስ ተወጥኖና ተከናውኖ የሚፈጸም ስለኾነ፡ ሰውኛውና ሰይጣናዊው፥ የዐውደ ነገሥቱና የልማዱ፥ የአማጩና የረማጩ፥ የሽምግልናውና የፍጥምጥሙ፥ የቃልና የጽሑፍ ውለታው፥ የሕጉና የሃይማኖቱ ውጣ ውረድና ግርግር ፈጽሞ አያስፈልገውም።

ከዚህ በኋላ፡ እናንተ፡ የአባታችሁ፡ የእግዚአብሔር እና የእናታችሁ፡ የእኔ የድንግል ማርያም ሙሽሮች ስለኾናችሁ፡ ሩካቤ ሥጋን ለመፈጸም እስከመፈለግ የሚያደርስ ፈቃድ ከተነሣሣባችሁ፥ ያ ፈቃዳችሁ፡ ጫጉላችሁ መኾኑ ነውና፡ በሰውኛው ሥርዓት፡ በሠርጋችሁ ዕለት እንዲፈጸም፡ ኹለታችሁ ካልተስማማችሁ በቀር፡ በማናቸውም ጊዜ ልትፈጽሙት ይቻላችኋል። እንዲህ ከፈጸማችሁትና ከዚያ ሩካቤ ሥጋችሁ፡ ሰው ከተፀነሰ፡ ያ ጋብቻችሁ፥ ያ መኻታችሁና ሩካቤ ሥጋችሁ፡ በእግዚአብሔር የተቀደሰና የተባረከ፡ ፍሬያማ መኾኑ መታወቁ፥ መገለጡና መረጋገጡም ነውና፡ ደስ ይበላችሁ! ከዚህ ተከትሎ የሚኾነው የኑሮ እውነታ፡ እንዲህ፡ በባልና ሚስትነት የተቀደሰ ጋብቻና ትዳር መሥርታችሁ የጀመራችሁትን፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕይወታችሁን፡ በይፋ መቀጠል ብቻ ነው።

ይኸው እግዚአብሔራዊው ሥርዓት፡ አማናዊና እውን መኾኑ፡ ከጋብቻው ጀምሮ፡ በሩካቤ ሥጋው በኩል አልፎ፡ እስከልጅ መውለዱ ድረስ፥ በአጠቃላይ፡ የትዳሩ ቤተሰባዊ ኑሮ፡ እንከን የሌለበት፡ ፍጹም ፍሬያማ በመኾኑ ይረጋገጣል። ይኸውም፡ ለዓቅመ አዳምና ለዓቅመ ሔዋን የሚደርሱበትን፡ የአካለ መጠን ዕድሜያቸውን ጠብቀው፡ በቅዱሱ ኪዳን የሃይማኖት ሥርዓት ከተጋቡ በኋላ፡ በዚህ ሕይወት የሚኖሩት ኪዳናውያኑ ኢትዮጵያውያንና ኪዳናውያቱ ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን፡ የቱንም ያህል የበዙ፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ቢወልዱ፡ በዚያ፡ ቤተሰባቸው ውስጥ፡ በነፍሳዊው፥ በሥጋዊውና በመንፈሳዊው ፍላጎታቸው በኩል፡ ምንም የሚጎድላቸው ነገር ሳይኖር፡ በኹሉም አግጣጫ ያገኙትና የሚያገኙት መለኮታው ጸጋና በረከት፡ የተሟላ ብቻ ሳይኾን፡ የተትረፈረፈ መኾኑ ጭምር ነው።

ደግሞም፡ ከእዚህ፡ እጅግ ተትረፍርፎ፡ ከሚታየው፡ የእግዚአብሔር ጸጋና በረከት በስተቀር፡ በእነዚያ፡ ጤናማና ሕያዋን ኾነው፡ በመልካም በሚያድጉት፥ ለዓቅመ አዳምና ለዓቅመ ሔዋን ዕድሜ ደርሰው፡ ለቍም ነገር በሚበቁት፥ በዘመናችሁም መሥፈርት፡ "ከመጠን በላይ በዝተዋል!" በሚባሉት ልጆቻቸው ምክንያት፡ ለዛሬው፡ ለተነሣንበት፡ "'ለወሊድ ቍጥጥር'፡ መንሥኤ ይኾናሉ!" የሚባሉት ችግሮች ኹሉ፡ ፈጽመው አለመኖራቸው ነው።

በአኹኑ ዘመናችሁ፡ ስታካኺዱትና ስትፈጽሙት የሚታየው፡ ይህን እግዚአብሔራዊዉን ሥርዓት፡ ማቃለልና ማግለል፥ እንዲያውም፡ መናቅና ማስወገድ፥ በእርሱም ቦታ፡ ለሰውኛውና ለሰይጣናዊዉ እውቀትና ፈሊጥ፡ ቅድሚያንና ብልጫን መስጠት፡ ነው።

እንዲህ አድርጋችሁ፡ "የወሊድ ቍጥጥር"ን ጨምራችሁ፡ የአሕዛብና የባዕዳን የኾነውን፡ ሌላውን ኹሉ በመተካታችሁ፡ ነፍሳዊውንና መንፈሳዊውን መልካም ህልውና ብቻ ሳይኾን፡ ሥጋዊውንና ምድራዊዉን ሳይቀር፡ ከማጣት መድረሳችሁ፡ ይኸው፡ በእውን እየታየ ባለውና እየጨመረ በሚኼደው ችግራችሁ፡ አረጋግጣችሁታል።

በዚህ ረገድ፡ እየራሳችሁን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ የጋብቻ ሕይወት ገና ያላበቃችሁ፡ አካለ መጠን ያደረሳችሁ፡ ወንዶችም፥ ሴቶችም ልጆቼ፡ በብዛት እንዳላችሁ አያለሁ። በዚህ የአዋጅ ቃሌ አማካይነት፡ ለእናንተ፡ የማስተላልፈው መልእክት፡ ተደጋግሞ እንደተነገራችሁ፡ **እየራሳችሁን፡ ለዚሁ፡ ለቅዱሱ ኪዳን፡ ኢትዮጵያዊ የጋብቻ ሕይወት እንድታበቁ ነው።** እስከዚያው ድረስ ግን፡ ይህንኑ፡ የ"ወሊድ ቍጥጥሩ"ን ግብር በሚመለከት፡ ከዚህ አስቀድሜ ከገለጽሁላችሁ እውነታ ጋር፡ በተጨማሪ ልታውቁት የሚገባችሁን ቍም ነገር አክልላችኋለሁ።

በእየዕድሜያችሁ፡ አካለ መጠን ያደረሳችሁ ደናግል፡ ወንዶችም፥ ሴቶችም፡ ጋብቻን እስክትፈጽሙ ድረስ፡ ከሌላው የጾታ ባልደረባችሁ ጋር፡ ሩካቤ ሥጋን ታደርጉ ዘንድ፡ የተፈጥሮ መልካም ግዳጅ የኾነው፡ ፍትወተ ሥጋችሁ (የሥጋችሁ ፈቃድ) እንደሚነሣሣባችሁ የታወቀ ነው። በዚህ ጊዜ፡ ይህ፡ ፍትወተ ሥጋችሁ፡ **የኃጢአት ስሜት መስኋችሁ፡ በውስጣችሁ ሁከት እንዳይፈጠርባችሁ መጠንቀቅ ይኖርባችኋል።**

በውስጣችሁ የተነሣሣባችሁ፡ ይህ፡ ፍትወተ ሥጋችሁ፡ እግዚአብሔራዊ የኾነው፡ መልካሙ የተፈጥሮ ጸጋ ስለኾነ፡ ደስ ብኋችሁ ተቀብላችሁት፡ በአግባቡ፡ ልታስተናግዱት ይገባችኋል እንጂ፡ ሰይጣናዊው አስተሳሰብና ሰብአዊው ልማድ በፈጠሩት ክፉው ጠንቅ፡ አዎን! የኃጢአት ስሜት መስኋችሁ፡ በውስጣችሁ ሁከት እንዳይፈጠርባችሁ መጠንቀቅ ይኖርባችኋል። ምግብ በማየት፥ ወይም፡ በረሃብ ምክንያት፡ በውስጣችሁ የሚፈጠረው፡ ማናቸውም ዓይነት፡ የመብል፥ ወይም፡ የመጠጥ ፍላጎት፡ ኃጢአት እንዳልኾነ ኹሉ፡ አዎን! ይህም፡ በውስጣችሁ የተነሣሣባችሁ፡ የሥጋችሁ ፈቃድ፡ እግዚአብሔራዊ የኾነው፡ መልካሙ የተፈጥሮ ጸጋ እንጂ፡ ሰይጣናዊው አስተሳሰብና ሰብአዊው ልማድ በፈጠሩት ክፉው ጠንቅ፡ የተገኘው ምትሓታዊውና ሓሳዊው፡ የኃጢአት ስሜት አይደለም።

እግዚአብሔራዊና መልካሙ የተፈጥሮ ጸጋ የኾነውን፡ ይህን፡ በውስጣችሁ የተነሣሣባችሁን፡ የሥጋችሁን ፈቃድ፡ በአግባቡ፡ ልታስተናግዱት የሚገባችሁ፡ እንዴት ነው? የመብሉንና የመጠጡን ጨምሮ፡ በየጊዜውና በየምክንያቱ፡ በውስጣችሁ የሚነሣሣባችሁን፡ ሌላውን፡ ማናቸውንም ዓይነት፡ የሥጋ ፍላጎታችሁን፡ በነፍሳዊውና በመንፈሳዊው አካላታችሁና ባሕርያታችሁ ኃይላት ተቆጣጥራችሁና ገርታችሁ፡ ተቋቁማችሁትና አለዝባችሁት፥ በመጨረሻም፡ አስተካክላችሁትና አሸንፋችሁት የለምን? እግዚአብሔራዊና መልካሙ የተፈጥሮ ጸጋ የኾነውን፥ ይህን፡ በውስጣችሁ የተነሣሣባችሁን፡ የሩካቤ ሥጋችሁንም ፈቃድ፡ እንደዚሁ፡ ተቆጣጥራችሁና ገርታችሁ፡ አዎን! ልትቋቋሙትና ልታለዝቡት፥ በመጨረሻም፡ ልታስተካክሉትና ልታሸንፉት ይቻላችኋል።

ለሥጋዊው ጤናማ ሕይወታችሁና መልካም ህልውናችሁ፡ በእጅጉ የሚያስፈልጋችሁን መብልንና መጠጥን፥ ይልቁንም፡ በተለይ የምትወድዱትን የምግብ፥ ወይም የመጠጥ ዓይነት እንኳ ሳይቀር፡ <u>በጾም መንፈሳዊ ኃይል፡</u> ሥጋችሁን ብቻ ሳይኾን፡ ነፍሳችሁን ጭምር፡ እንዴት አድርጋችሁ ተቈጣጥራችሁ፡ ድክመታችሁንና ተጠቂነታችሁን አስወግዳችሁ፡ ዕሩቅ ብእሲነታችሁን (ተራ ሰውነታችሁን)፡ ወደፈለጋችሁት ሉዓላዊና ሰላማዊ የፍቅር ግብ ለማድረስ እንደቻላችሁ፥ በዚህ፡ የዘወትር ሃይማኖታዊ ምግባራችሁ ጭምር፡ ለእየራሳችሁ፡ በቀላሉና በእርግጥ አስመስክራችኋል።

ይህን እውነታ፡ እስኪ፡ በእናትነት ቃሌ፡ በጥቂቱ ላብራራላችሁ! የማብራራላችሁም፡ ከዚህ አስቀድሜ፥ አኹንና ከዚህ በኋላ፡ ከእናንተ፡ ከወንዶቼና ከሴቶቼ፥ ከኹላችሁም ልጆቼ ጋር፡ በእየፊናችሁም ኾነ በጋራ በማደርገው ንግግር ረገድ፡ ይኸው፡ ከአዋጅ ቃሌ እንደምትሰሙት፥ ከጽሑፉም እንደምትመለከቱት፡ በምትኖሩበት፡ በሰውኛው ልማድ፡ በየጾታችሁ፡ የየግል ምሥጢራችሁ አድርጋችሁ በምትይዙት ጉዳይ ውስጥ ኹሉ ሳይቀር፡ በፍጹም ግልጽነት ላዋያችሁ በመፈለጌ ነው፤ የዚህንም ምክንያት፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ ከእኔ እናትነት ይልቅ፡ የበለጠ ቅርበትና ፍቅር ያለው፡ ወላጅና ቤተሰብ፥ ቤተ ዘመድና ወዳጅ፥ ወይም ባልንጀራና ባልደረባ፡ ለእናንተ ለልጆቼ የሌላችሁ መኾኑን፡ እኔ የማውቀውን ያህልም ባይኾን፡ እናንተም፡ እያንዳንዳችሁ፡ እንደየዓቅማችሁ፡ በሚበቃ እንደምትገነዘቡት እረዳዋለሁ።

በዚህ መልክና ይዘት፡ ለአብነት ያህል ያነሣሁትን፡ የመብልንና የመጠጥን ነገር ለመቀጠል፡ ከእናንተ መካከል፡ ጣዕም ያለውን መጠጥ የመጠጣት፡ ብርቱ ፍላጎት ያደረባችሁ፡ ምናልባት፡ አንዳንዶች ብትኖሩ እንኳ፡ ይህንኑ፡ ኃይለኛ የወይን፥ ወይም፡ የማር ጠጅን አብዝታችሁ ከጠጣችሁ፡ እንደምትሰክሩ ስለምታውቁ፡ ተገቢውን መጠን ጠብቃችሁ፥ በመለኪያም ለክታችሁ ለመጠጣት፥ እንዲያውም፡ ጨርሶ ላለመጠጣት፥ ይህንም፡ እጅግ ጽኑ የኾነውን፡ የሥጋን ፍትወት (ፈቃድ)፡ በጠንካራው መንፈሳዊ አካላችሁና ባሕርያችሁ ኃይል፡ እንዲህ ተቆጣጥራችሁ፡ ለመቋቋምና ለማሸነፍ እንደሚቻላችሁ፡ አረጋግጣችኋል።

ጥምባሆም፡ የሳምባ ነቀርሳ በሽታን እንደሚያስከትል ስላወቃችሁ፡ የልጅነት ጨቅላነት፥ ወይም፡ የጕልምስና ግለት ቢገፋፋችሁም እንኳ፡ ላለማጤስ መወሰን እንደሚቻላችሁ፡ ተረድታችኋል። የሩካቤ ሥጋ ፍትወትንም፡ "በዚህ መልክና ይዘት፡ ተቆጣጥራችሁ፡ ለመቋቋምና ለማሸነፍ ይቻላችኋል!" ማለት ነው።

ምናልባት፡ ይህን ኹሉ ተጋድሎ፡ በጾምና በጸሎት፥ በስግደትም ጭምር ፈጽማችሁት፡ አኹንም፡ የሩካቤ ሥጋ ፍላጎታችሁን ነበልባል ለማቀዝቀዝ፥ የማዕበሉንም ኃይል፡ ለማረጋጋት ሳትችሉ ብትቀሩ፡ በመሠረታዊው እግዚአብሔራዊ ተፈጥሮው፡ መልካም የኾነው፡ ይህ የጋለና የጸና ስሜታችሁ፡ እንዲህ እየጠነከረ የኼደበት፡ አንዳች የተለየ፡ መንፈስ ቅዱሳዊ ምክንያት እንደሚኖረው መገንዘብ ይኖርባችኋል።

ከዚህ በኋላ፡ በዚህ አቋም ኾናችሁ፡ ሩካቤ ሥጋውን፡ ከኃጢኣት ስሜት በጸዳ፡ በንጹሕ ፍቅር ለመፈጸም፡ ዒላማ የኾነውን ተነጻጻሪውን የጾታ ወገናችሁን፡ በቀጥታ ኼዳችሁ፡ ፊት ለፊት በመገናኘት፥ በእግዚአብሔር ስምና እውነት፡ በግልጽ በማነጋገርም፡ ግቡ፡ ጋብቻ የኾነውን ግንኙነት፡ በዚህ ኹኔታ መጀመር ይቻላችኋል።

ይህን የመሰለው የተቀደሰ የጽድቅ ስሜት፡ የቅዱሱ ኪዳን ታማኝ በኾነው ሰውነታችሁ ውስጥ፡ በጽናት የሚነሣሣው፥ የተነሣሣውም፡ ያለበቂና ያለመልካም ምክንያት፡ እንዲያው በከንቱ አለመኾኑን መረዳት፥ ይህም መነሣሣት፡ የፍትወቱ ስሜት ፈጣሪ በኾነው፡ በራሱ፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደኾነ ማመን ይገባችኋል።

ይህ ስሜት፡ በውስጣችሁ የተቀሰቀሰው፥ እየተጠናከረም የኼደው፡ "መጨረሻውና ውጤቱ፡ ሕያው ለኾነ፡ ለአንድ መልካም ዓላማ ነው!" ብሎ፡ በዚያ ታማኝ ኪዳናዊ ሰውነታችሁ ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ፡ በእርግጥ ያሳስባችኋል፤ ያ፡ ሕያው የኾነው፡ መልካሙና ዘለዓለማዊው ዓላማ፡ ጋብቻ እና/ወይም፡ በእግዚአብሔር መልክ የሚፈጠረውንና "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" የሚባለውን ሰብኣዊውን አካልና ባሕርይ ለማስገኘት የተዘጋጀው መለኮታዊ ዕቅድ የሚፈጸምበት ግንኙነት መኾኑ ነው።

ለነገሩ፡ ጥንቱኑም ቢኾን፡ እግዚአብሔርን መስሎና አኽሎ የሚወለደውን፥ ሰውን የሚያህል ሕያው ፍጡር የሚያስገኘውን፡ ያን፡ የፍትወተ ሥጋ ባሕርያዊ ስሜት፥ አካላዊነት ያላቸውን፡ የወንዱን ዘርና የሴቲቱን የወር አበባ ጨምሮ የያዘው፡ የሥነ ፍጥረት ድንቅ ምሥጢር፡ እጅግ የተዋበና የጣፈጠ፥ ንጹሕና ቅዱስ መኾኑ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታችሁ ያረጋገጣችሁት ነው።

ተደጋግሞ እንደተገለጸው፡ ፈጣሪ ራሱ፡ ፍጹም መልካም አድርጎ እንደፈጠረው፡ እንደሌላው ፍጥረት ኹሉ፡ አዎን! ይህም፡ የሩካቤ ሥጋ፡ የፍትወት፡ ባሕርያዊ ስሜት፥ አካላዊነት ያላቸውን፡ የወንዱን ዘርና የሴቲቱን የወር አበባ ጨምሮ የያዘው፡ የሥነ ፍጥረት ድንቅ ምሥጢር፡ እጅግ የተዋበና የጣፈጠ፥ ንጹሕና ቅዱስ ነው።

ይህን፡ በመለኮታዊው የሥነ ፍጥረት ድንቅ ምሥጢር፡ እጅግ የተዋበና የጣፈጠ፥ ንጹሕና ቅዱስ ኾኖ የተሠራውን፡ የፍትወተ ሥጋ ባሕርያዊ ስሜት፡ "ኃጢኣት ነው!" ብሎ፡ በኃጢኣትነት መፈረጅ፡ ራሱን ሠሪውን እግዚአብሔርን፡ መንቀፍና በሓሰት መወንጀል፥ መስደብም ነው። በዚህ ጊዜ፡ ያ፡ ይህን የመሰለውን ድፍረት የፈጸመው ሰብኣዊ ፍጡር፡ ራሱ ሰይጣን ኾነ ማለት ነው፤ ለዚህ ድርጊቱም፡ እንደልጁ ወዳጁ ኢየሱስ መሢሕ ቃል፡ በመለኮታዊዋ የፍርድ ቀን፡ መልስ በመስጠት፡ ፍዳውን እንደሚቀበል፡ ሃይማኖታዊው እውነት አረጋግጦላችኋል። (ማቴ ፲፪፥ ፳፬-፴፯።)

ይህ እውነታ፡ እግዚአብሔር የፈጠረውን የእንስሳና የአውሬ፥ የወፍና የዓሣ ዓይነት ኹሉ፡ መልአኩ፡ በራእይ፡ ከሰማይ አውርዶ አቅርቦለት፡ "ተንሥእ! ኀርድ! ወብላዕ!" ፡ "ተነሥተህ፥ ዐርደህ ብላ!" ባለው ጊዜ፡

"ሐሰ ሊተ! እግዚኦ! ግሙራ፡ ኢቦአ ርኵስ ውስተ አፉየ፤ ወኢበላዕኩ፡ ዘኢኮነ ንጹሐ።" ፡ "ጌታ ሆይ! አይኾንም፤ አንዳች ርኵስ፥ የሚያስጸይፍም፡ ከቶ በልቼ አላውቅምና!" ሲል መልስ በመስጠቱ፡

"ዘእግዚአብሔር አንጽሐ፡ አንተ ኢታስተራኵስ!" ፡ "እግዚአብሔር ያነጻውን፡ አንተ አታርክሰው!" የሚል ሰማያዊ ግሣፄን፡ ሦስት ጊዜያት በተቀበለው፥

ከዚህም በላይ፡ ቀደም ብሎ፡ በመምህሩ፡ በልጇ በወዳጇ በኢየሱስ መሢሕ ፊት፡ የትስብእትን የመስቀል መከራ በመቃወሙ፡ በመለኮታዊው አንደበት፡ "ሑር እምድኅሬየ ሰይጣን!" ፡ "አንተ ሰይጣን! ከኋላዬ ወግድ!" ተብሎ በተዘለፈው፡ በሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ተደጋጋሚ ድርጊቶች፡ ተከሥቶ ታይቷል። (የሐዋ. ፲፥ ፱-፲፮። ማቴ. ፲፮፥ ፳፩-፳፫።)

ራሱ፡ "ሐሰት፣ የሐሰትም አባት" መኾኑ፡ በልጇ በወዳጇ በኢየሱስ መሢሕ ቃል የተነገረበት፡ ዲያብሎስና የእርሱ ጭፍሮች የኾኑ ክፉዎች ሰዎች፡ ይህን፡ <u>የሩካቤ ሥጋን፡ ባሕርያዊ የፍትወት ስሜት፥</u> ኾን ብለው፡ በሐሰትና በተንኰል፡ "ኃጢአት ነው!" ብለው፡ በኃጢአትነት ፈረጁት እንጂ፡ ኃጢአት አለመኾኑን፡ እንኳንስ፡ እናንተ ልጆቼ፡ ማንኛውም፡ ሰብኣዊ ፍጡር፡ በተስተካከለ አእምሮው ካስተዋለው፡ በቀላሉ፡ ከእውነቱ ለመድረስ እንደማያዳግተው መገንዘብ ይቻለዋል፤ "ሃይማኖታዊውን አስተሳሰብ ሳይቀር፡ ወደጎን አስቀምጦ፡ ልማዳዊዉን የተፈጥሮ ሥርዓት ብቻ እንኳ፡ እግምት ውስጥ በማስገባት" ማለት ነው።

ይህ ዘይቤ፡ እንዲህ በሚል አገላለጽ፡ ሊብራራላችሁ ይቻላል፦ ሕያው ነፍስ ያለው ማንኛውም ፍጡራችን፡ ፈጣሪው እግዚአብሔር፡ በደነገገለት የተፈጥሮ ሥርዓት፡ በሕይወቱና በህልውናው ለመቀጠል ሲል፡ መብሉንና መጠጡን፡ መርጦና መጥኖ ይበላል፤ ይጠጣልም። ይህ፡ የፍጡራችን፡ የመብላትና የመጠጣት ድርጊት፡ መቼም፡ በእውነተኛውም ኾነ በሐሰተኛው ሰብኣዊው ፍጡራችን ዘንድ፡ "ኃጢአት ነው!" ተብሎ፡ በኃጢአትነት የሚፈረጅ አይደለም።

እንደዚሁ ኹሉ፡ ያ ፍጡራችን፡ ያንኑ፡ የተፈጥሮውን ሥርዓት ተከትሎ፡ በመብሉና በመጠጡ ምክንያት፡ የሚደርስበትን፡ የመጸዳዳት ግዳጅ ይፈጽማል፤ ይህንኑ ግዳጅ በሚፈጽምበት ጊዜ፡ ይኼም ግዳጅ፡ እንደቀደመው ኹሉ፡ በኹሉም ወገኖች ዘንድ፡ "ኃጢአት ነው!" ተብሎ፡ በኃጢአትነት እንደማይፈረጅ፡ በኹሉም ዘንድ ይታወቃል። በእንስሳቱና በአራዊቱ፥ በአዕዋፉቱና በዓሣቱ ዘንድ እንደሚፈጸመው የተፈጥሮ ሥርዓት ኹሉ።

የሰውኛ የኾነው፡ የእናንተ ወገን፡ ከእንስሳቱና ከአራዊቱ፥ ከአዕዋፋቱና ከዓሣቱ የሚለይበት ኹኔታ፡ ይህን፡ እግዚአብሔራዊዉን የተፈጥሮ ሥርዓትና ግዳጅ፡ በእግዚአብሔር መልክ በተፈጠረበትና በመለኮታዊው ቃል፡ "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" በተባለበት፡ መንፈስ ቅዱሳዊ የልዕልና አካሉና ባሕርዩ፡ ተቈጣጥሮና አስተካክሎ፡ ለሚጠበቅበት ፍጹምነት ለማብቃት፡ የመቻሉ እውነታ መኾኑን፡ ኹላችሁም ልጆቼ የምታውቁት ነው።

ራሱ፡ የመለኮት፡ ዕፁብ ድንቅ ሥራ የኾነው፡ ይህ የሰውነታችሁ ሥጋዊ አካልና ባሕርይ፡ የሚሠራውን ዕፁብ ድንቅ ሥራ ደግሞ ተመልከቱት! እናንተው እየራሳችሁ፡ "እንከን የሌለበት፥ ፍጹም ጥሩ ነው!" ብላችሁ፡ አሳምራችሁና አጣፍጣችሁ ከሠራችሁት፥ እንዲሁም፡ "ያስፈልገናል!" ብላችሁ፡ ሳስታችሁና ጥሟችሁ ከበላችሁት መብልና ከጠጣችሁት መጠጥ ላይ፡ የሚያስፈልገውንና የሚበቃውን መልካሙን ብቻ አስቀርቶ፡ ሌላውን፡ የማያሻውን ዝቃጩን፡ ለዚያ፡ ለራሱ ለሰውነታችሁ፡ የሚያስጸይፍ እስከመኾን በደረሰ ጎሰርነት፡ ከሰውነታችሁ እንዲወጣ ያደርገዋል።

እዚህ ላይ፡ በእናንተም ዘንድ ቢኾን፡ ሊጤን የሚገባውና ከዚህ ጋር የተያያዘው ቍም ነገር፡ ለዚያ በላተኛና ጠጪ ፍጡር፡ መልካም ሕይወትና ጤናማ ህልውና መቀጠል፡ ያ የመጸዳዳቱ ግዳጅ፡ በግዴታም ኾነ በውዴታ፡ በአግባቡና በጊዜው መፈጸም እንዳለበት ነው። ሳይፈጸም ቢቀር ግን፡ ውጤቱ፡ በዚያ ፍጡር ላይ፡ ወደሞት የሚያደርስ፡ የጽኑ በሽታን ጠንቅ ሊያስከትልበት እንደሚችል ይታመናል።

ያለው እውነታ፡ ይህ ከኾነ ዘንድ፡ <u>የሩካቤ ሥጋ፡ ፍትወታዊ ስሜትም</u> የመጣው፡ ከነፍሳዊውና ከመንፈሳዊው የተፈጥሮ አካላትና ባሕርያት ጋር፡ በሥጋዊነቱ፡ ከዚሁ፡ ከመብሉና ከመጠጡ በመኾኑ፡ እርሱም፡ እንደመብሉና እንደመጠጡ የመጸዳዳት ሥርዓታዊ ግዳጅ፡ በከያኒው ፈጣሪ ጥበብ በተዘጋጀለት ባሕርያዊ መገለጫና አባለዘር አማካይነት፡ ከዚያ ሰብአዊ ፍጡራችን ሰውነት፡ በአግባቡ ሊወጣ እንደሚገባው፥ እንደሚያስፈልገውም፡ ኹላችሁም፡ የምታውቁት ነው።

ይህ ሊኾን እንደሚገባውና እንደሚያስፈልገውማ፡ የተፈጥሮው ሥርዓት፡ በዚሁ አስገዳጅ መልኩና ይዘቱ እየመሰከረና እያረጋገጠ ያስገነዝባል። አለዚያ፡ ያ፡ የመጸዳዳቱ ግዳጅ፡ እንዳይፈጸም ቢደረግ፡ ያ ሰብአዊ ፍጡራችን፡ "እስከሞት ያደርሳል!" ለተባለው፡ የደዌ ጠንቅ እንደሚጋለጥ ኹሉ፡ በዚህም ረገድ፡ የሩካቤ ሥጋው ፍትወት፡ በግድ፡ እንዲገታ ቢደረግ፡ በዚሁ ሰብአዊ ፍጡራችን ላይ፡ አንዳች፡ የአካልና የባሕርይ፥ የምግባርም ቀውስ፡ ማድረሱ አይቀርም። ባልበቁት መነኮሳት ላይ ደርሶ እንደሚታየው።

እንግዴህ፡ እግዚአብሔራዊ የኾነውን፡ ይህን፡ መልካሙን የተፈጥሮ ሥርዓት ነው፡ ክፉዎች፡ ከነአካላቱና ባሕርያቱ፥ ምግባሩ ጭምር፡ ባጠቃላይ፡ "ኃጢአት ነው!" ብለው፡ በኃጢአትነት የፈረጁትና በንጽሓ ጠባይ የተፈጠራችሁትን፡ እናንተን ልጆቼን፡ ለቀውስና ለሥቃይ ሊዳርጉ የቻሉት።

ይኸው፡ የመብላቱና የመጠጣቱ፥ ከዚያም፡ የመጸዳዳቱ ተግባርና ግዳጅ፡ እግዚአብሔራዊዉን የተፈጥሮ ሥርዓት ተከትሎ የሚፈጸም በመኾኑ፡ "መልካምና ተገቢ ነው!" ተብሎ፡ በፍጡራኖቻችን ኹሉ ዘንድ፥ በክፉዎቹም ሰዎች ዘንድ ሳይቀር፡ ልዩ ክብርና ማዕርግ ተሰጥቶት፡ ያለችግር የሚስተናገድ ሲኾን፡ <u>የተፈጥሮ ባሕርይ የኾነው፡ ይህ፡ የሩካቤ ሥጋ ፍትወት</u> ግን፡ ያለበደሉና ዕዳው፡ "ኃጢአት" ተብሎ፡ ጠንቀኛና አጣብቂኝ ከኾነ ጽኑ ቀውስ ውስጥ፡ ይኸው ተዘፍቆ ሲታወክ ይኖራል።

ለዚህ ክፉ ኹኔታ፡ ዘላቂ መፍትሔ የሚኾን፡ ሌላ ማማረጫ የለም። ምንኵስናም እንኳ፡ ማማረጫ ሊኾን አልቻለም። ቢኖርም፡ ይኸው፡ በሰዎች ዘንድ ታስቦ የተሠራው፡ "የወሊድ ቍጥጥር" የተባለው ብቻ ኾኖ መገኘቱ፡ ቀውሱን የበለጠ አባብሶታል እንጂ፡ አላሰከነውም። ምክንያቱም፡ ሥጋዊው የመጸዳዳት ግዳጅ፡ እስከመጨረሻው ቢከለከል፡ ለዚህ ጭካኔና ግፍ፡ የሚዳረገውን፡ ያን ሰብአዊ ፍጡራችንን የሚጠብቀው፡ ወደሥጋ ሞት የሚያደርሰው አሠቃቂው የሥጋ ደዌ ብቻ እንደሚኾን ኹሉ፡ <u>የሩካቤ ሥጋ ፍትወትም፡</u> በተፈረጀበት፡ በኃጢአት ገጽታው እውቅናንና ተቀባይነትን አግኝቶ፡ ይኸው፡ በዚሁ መልክና ይዘት በመከልከሉ፡ በሰብአዊው ፍጡራችን ላይ ያስከተለው ሥቃይ፡ እጅግ የበዛና የከበደ፥ የጠለቀና የረቀቀ ኾኖ መቀጠሉ በገሃድ ስለሚታይ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ ክፉውን (ሰይጣናዊዉን) "የወሊድ ቍጥጥር" የመረጠውን ሰብአዊዉን ፍጡራችንን የጠበቀው፡ ይኸው፡ አኹን፡ በምድር ላይ፡ እየደረሰበት ያለው፡ ወደሥጋ ሞት የሚያደርሰው፡ አሠቃቂው የሥጋ ደዌ ብቻ አይደለም፤ በይበልጥና በተጨማሪ፡ በዘለዓለማዊነት ወደሚቀጥለው፡ ወደነፍሳዊዉና መንፈሳዊው የሞት ፍዳ የሚያደርሰው፡ ሥጋዊው፥ ነፍሳዊውና መንፈሳዊው የፈተና ሥቃይ ጭምር እንጂ። በዚህም፡ በገዛ ፍላጎቱና ምርጫው ለባዘነው፡ ለዚሁ ከርታታ ሰብአዊ ፍጡራችን የተረፈው፡ ሦስቱ አካላቱና ባሕርያቱ ለኾኑት፡ ለሥጋው፥ ለነፍሱና ለመንፈሱ፡ እውነተኛውን ደስታና ሰላማዊዉን ዕረፍት አጥቶ፡ እንደእሳት እያነደደውና እንደማዕበል እያማታው ባለው፡ በፍርሃትና በጥርጣሬ፥ በሥጋትና በጭንቀት መከራው ውስጥ፡ እየማቀቁ መኖር ኾኖ ይገኛል።

## ቅዱሱ ኪዳን፡
## ለምስክርነት የሚያቀርባቸው፡ የአብነት ማስረጃዎች።

እዚህ ላይ፡ ወንድ እና ሴት፡ በምክንያት ተዋውቀው እንዲገናኙና የሩካቤ ሥጋ ግዳጅን እንዲፈጽሙ፡ በተፈጥሮ ሥርዓቱን የሠራ፥ ያም ሥርዓት፡ በተግባር ላይ ውሎ፡ ኹለቱ ጾታዎች እንዲባዙ፥ መካን የኾኑ አብራክን በማለምለምና ማሕፀኖችን በመክፈት ጭምር፡ ለፍሬ እንዲበቁ፥ የሚያደርግ፡ እግዚአብሔር ስለመኾኑ፡ ለዚህ ታላቅ ሃይማኖታዊ ቍም ነገር፡ አብነት የሚኾኗችሁን ማስረጃዎች፡ ለምስክርነት፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት ሊጠቀሱላችሁ ይቻላል። እነዚህም፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፦

በሥጋዊው የፍትወት ስሜታቸው፡ ሙታን ለነበሩት፡ በአንድ ወገን፡ በብሉዩ ኪዳን ዘመን፡ ይስሓቅን ለወለዱት፡ ለመቶ ዓመቱ ሽማግሌ፡ ለአብርሃምና ለዘጠና ዓመቷ አረጋዊት ሚስቱ፡ ለሣራ፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ በአዲስ ኪዳኑ ዘመን፡ መጥምቁ ዮሓንስን ለወለዱት፡ ለአረጋዊው ካህን፡ ለዘካርያስና ለአሮጊቷ ሚስቱ፡ ለኤልሣቤጥ፡ አስፈላጊውን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት እንዲያደርጉና እንዲፈጽሙ፡ እግዚአብሔር፡ የሙሽርነታቸውን ተፈጥሮአዊና ተአምራዊ የፍቅር ስሜትና ኃይል፡ መልሶ እንዳሳደረባቸው ታውቃላችሁ።

ይህ ብቻ አይደለም፤ "የእግዚአብሔር ወዳጅ!" የተባለው፥ ከእርሱ፡ ከፈጣሪውም ጋር፡ ባለቃል ኪዳን ተዋዋይ ለመኾን የበቃው፡ ይኸው፡ የመቶ ዓመቱ ሽማግሌ አብርሃም፡ ከሚስቱ ከሣራ፡ ይስሓቅን ከመውለዱ በፊት፡ ሚስቱ ካልኾነችው፡ ከአጋር ጋር፡ የመኝታና የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት አድርጎ፡ የመጀመሪያ ልጁን፡ እስማኤልን በወለደ ጊዜ፡ ይህ ድርጊቱ፡ በእነርሱ፡ በባልና ሚስቱ፥ በኅብረተሰባቸውም ዘንድ፥ በእግዚአብሔርም ዘንድ ሳይቀር፡ እንደኃጢአት እንዳልተቆጠረ፥ "ኃጢአት ነው!" ተብሎም፡ በቃል እንዳልተነገረ፥ በብራና ላይ ተጽፎም፡ በኃጢአትነት እንዳልተፈረጀ፥ ታውቃላችሁ። አዎን! ይህ ኹሉ፡ ጨርሶ "ኃጢአት" ስላልኾነ ነው።

በሓሰት፡ "ኃጢአት ነው!" ብለው፡ በኃጢአትነት የፈረጁት፡ ራሳቸው፡ "ኃጢአት"፡ የኾኑት፡ ዲያብሎስና የእርሱ ጭፍሮች የኾኑ፡ ክፉዎች ሰዎች ናቸው። "ኃጢአት" ማለት፡ የቃል ለቃል ትርጉሙ፡ "ኃጢአ-ጽድቅ"፥ ማለት ነው፤ "እውነትን ያጣ"፥ "እውነት የሌለችበት" ማለት ነው፣ እርሱም፡ "ሓሰት" ተብሏል። ስለዚህ፡ "ሓሰት"፡ የ"ኃጢአት" ሌላው ስሙ መኾኑን፡ በማስተዋል ተመልክታችሁ፡ ምንጊዜም፡ በእውነተኛ ምንነቱ፡ ልታጤኑት ይገባችኋል።

እውነታው ይህ በመኾኑ እኮ ነው፡ ሽማግሌው አብርሃም፡ የሚስቱ የሣራ ገረድ ከኾነችው፡ ከግብፃዊቷ ከአጋር ጋር፥ ከጋብቻ ውጪ፡ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ፡ የፈቃደኛነቱና የፍላጎቱ ስሜት፡ በዚያ የእርጅና ዕድሜው የተነሣሣበት፤ የዐየለበትም። ይህን ስሜት መፍጠር፥ ኃይሉን መስጠትና ድርጊቱንም እንዲፈጽም ማድረግ የሚቻለውና የተቻለው፡ እግዚአብሔር ነው። እንግዲያ! ያ እውነተኛ ኹኔታ፡ ምንጊዜም፡ በኪዳናዊና በኪዳናዊት የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ የማይኖርበት፥ የማይፈጸምበትም፡ ምንም ምክንያት የለም።

ሣራ፡ በመቶ ሃያ ሰባት ዓመቷ ከሞተች በኋላ፡ "ሸመገለ፤ በዘመኑም አረጀ፤ ዐፈጀ፤" የተባለው፡ ይኸው፡ አብርሃም፡ ቀድሞ፡ ራሱ፡ ከመልከ ጼዴቅ፥ ኋላም፡ ከመልከ ጼዴቅ የትውልድ ሓረግ ከሠረፀችው፡ ከኢትዮጵያዊቷ ኬጡራ ባገኘው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱ፡ እርሷን አግብቶ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችንን የወለደው፡ በስንት ዓመቱ መኾኑን ለመገመት፡ ለማናችሁም የሚሳናችሁ አይደለም።

እነርሱም፡ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር በኾነችው፡ "ምድያም" በተባለችው ምድር ስለሚኖሩ፡ "ምድያማውያን" የተባሉት ናቸው።

ደግሞስ፡ **"ኢይኩን እንከ ስምከ፡ 'ያዕቆብ!' ዳዕሙ፡ ይኩን ስምከ፡ 'እስራኤል!' እስመ ክህልከ፡ ምስለ እግዚአብሔር፥ ወምስለ ዕጓለ እመሕያው።"**

**"ከእንግዲህ ወዲህ፤ ስምህ፡ '‹እስራኤል› ይባል እንጅ፡ ‹ያዕቆብ› አይባል! ከእግዚአብሔር፥ ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና!'** የተባለው ያዕቆብ፡ "ራሔል" እና "ልያ" ከተባሉት፡ ኹለት ሚስቶቹ፥ "ዘለፋ" እና "ባላ" ከተባሉት፡ ከእነርሱ ኹለት ገረዶቹም፡ ፲፪ (አሥራ ኹለት) ልጆችን ሲወልድ፡ ይህ ድርጊቱ፡ ኃጢኣት አልኾነበትም፤ በራሱም፥ በቤተሰቡና በወገኖቹ፥ በእግዚአብሔርም ዘንድ፤ እንደመልካም እንጂ፡ እንደጥፋት፥ እንደበረከት እንጂ፡ እንደኃጢኣት አልተቆጠረበትም።

ይህም ኾኖ፡ **"እንደአዳምና ሔዋን፡ አንድ ወንድ፡ ለአንዲት ሴት፥ አንዲት ሴት፡ ለአንድ ወንድ"፡** የሚለውን፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓተ ጋብቻ አክብራችሁና አጽንታችሁ በምትኖሩት፡ በእናንተ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ ዘንድ፡ ይህ፡ የያዕቆብ አድራጎት፡ ቅዱሱን የኢትዮጵያዊነትን የጋብቻ ቃል ኪዳን እንደማፍረስ ስለሚቆጠር፡ እንኳንስ፡ ሊፈጸም፡ ጭርሱኑም አይታሰብም።

በዚህ ረገድ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ ፈጽሞ የበቃው፡ እስራኤላዊ የነበረው ሙሴ፡ ወደኢትዮጵያ መጥቶና በዚያ ኖሮ፡ ኹለት ልጆችን ከወለደችለት፡ ከኢትዮጵያዊቷ ሚስቱ፡ ከሲጳራ ጋር በፈጸመው ጋብቻውና የትዳር ኑሮው ምክንያት፡ ከእስራኤላውያኑ ወገኖቹ የደረሰበትና እናንተም የምታውቁት የተቃውሞ ፈተና፡ እዚህ ላይ ሊወሳ ይገባዋል። እርሱም፡ ሙሴ፡ በዚሁ ኢትዮጵያዊነቱ፡ ያለውልውል ከመጽናቱ የተነሣ፡ እስራኤላዊቷ እኅቱ፡ ሚርያምና እስራኤላዊው ወንድሙ አሮን ሳይቀሩ፡ የእስራኤል ልጆች፡ በጠላትነት ተነሥተውበት፡ በእግዚአብሔር ቍጣና መቅሠፍት እንደተገሠፁ የሚያረጋግጠው ዝክረ ነገሩ ሲኾን፡ ያም፡ በዘመኑ ዜና መዋዕል ተጽፎ፡ እነሆ እስከዛሬ ይነበባል።

በመጨረሻ፡ **"ረከብክዎ፡ ለዳዊት ወልደ እሴይ፤ ብእሴ ምእመነ ዘከመ ልብየ፤ ዘይገብር ኵሎ ፈቃድየ።" ፤ "የልቤን አሳብ ትከትሎ፡ ፈቃዴን ኹሉ የሚፈጽም፡ ታማኝ ሰውን፥ እርሱም፡ የእሴይ ልጅ ዳዊትን አገኘሁ!"** ብሎ፡ እግዚአብሔር የመሰከረለትንና ለማካተቻው ፯ኛ ቃል ኪዳኑ ተዋዋይ ያደረገውን፡ ጻድቁን ነቢይ፡ ንጉሥ ዳዊትን በሚመለከት፡ በዚህ ረገድ፡ እዚህ ላይ ሊታከል የሚገባው፡ ሌላ ዝክረ ነገር አለ።

ያም፡ ወራሴ መንግሥቱ የኾነው፡ ልጁ፡ ንጉሥ ሰሎሞን ያደረገው ይቅርና፡ ራሱ፡ አባትዮው፡ ንጉሥ ዳዊት፡ ከብዙ ሚስቶቹና ቁባቶቹ፡ ብዙ ልጆችን መውለዱ ሳያንስ፥ ያም፡ እንደኃጢኣት ሳይቈጠርበት፥ ሌላው፡ በድፍረት የፈጸመውን፡ ታላቁን ግፍ የሚያወሳው ነው።

የዳዊት ታላቁ ግፍ፡ በጦር ግዳጅ ላይ ተሠማርቶ፡ እየተጋደለ ያለውን፡ የታማኝ አገልጋዩን፡ የኢትዮጵያዊዉን፡ የኦርዮንን፡ አንዲት የቃል ኪዳን ኢትዮጵያዊት ሚስት፡ ቤትሳባን፡ በሥውር መድፈሩ ብቻ ሳይኾን፡ እርሱን ባሏን፡ በግፍ ተንኰል ካስገደለ በኋላ፡ እርሷን፡ በገሃድ፡ ሚስት በማድረግ፡ የፈጸመው፡ ወደር የሌለው በደል ነው። ያን የመሰለው ከባድ ጥፋት፡ በንስሓ ምሕረት ተወግዶና እንዳልተፈጸመ ተቆጥሮ፡ መለኮታዊው ፈቃድና ዕቅድ፡ እስከመጨረሻው እንደቀጠለ ታውቃላችሁ።

የአብርሃም የወንድም ልጅ የኾነው ሎጥም፡ ከኹለት ሴቶች ልጆቹ መውለዱ፡ እንዲሁ፡ እንደኃጢአት ሳይቆጠር፡ ከእነርሱ፡ የዘር ሓረግ የተወለደችው፡ ሩት፡ የዳዊትን ቅድመ ቅድም አያት የኾነውን፡ ቦኤዝን አግብታ፡ ለቃል ኪዳኑ፡ ዘለዓለማዊ ንጉሠ ነገሥት፡ ለኢትዮጵያዊው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቅድመ ቅድም አያትነት በቅታለች። (ዘፍጥ. ፩፥ ፳፯-፳፰፤ ፪፥፲፰-፳፭። ፲፯፥ ፩-፲፯፤ ፲፰፥ ፲፭-፲፰፤ ፳፫፥ ፩-፪፤ ፲፱፥ ፴-፴፰፤ ፳፬፥ ፩፤ ፳፭፥ ፩-፰፤ ፳፱፥ ፲፫-፴፭፤ ፴፥ ፩-፳፬፤ ፴፪፥ ፳፪-፴፪። ዘኍ. ፲፪፥ ፩-፲፭። ሩት ፪፥ ፩-፪፤ ፬፥ ፲፫-፳፪። ፪ኛ ሳሙ. ፲፩፥ ፩-፳፯፤ ፲፪፥ ፩-፴፩። ማቴ. ፩፥ ፩-፮። የሐዋ. ፲፫፥ ፳፪።)

እነዚህ ኹሉ ዝክረ ነገሮች፡ አረጋግጠው የሚመሰክሩት፡ ይህን ኹሉ የድርጊት ሥርዓታዊ ኺደት፡ የፍጥረቱ ሠሪና ባለቤት የኾነው እግዚአብሔር፡ ሳያውቀውና ሳይፈቅደው ሊወጠን፥ ሊካኼድና ሊከናወን እንደማይችል ነው። ይኸውም፡ በሰብአውያን ፍጡራን ዘንድ፥ ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" በተባሉት ዘንድ፡ በጋብቻም ኾነ ከጋብቻ ውጪ፡ ለሰው ልደት፡ መነሻ ምክንያት የኾነው፥ በወንድና በሴት መካከል የሚደረገው፡ በመጀመሪያ፡ መተያየቱ፥ ትውውቁና መነጋገሩ፥ ከዚያም፡ ለመቀራረብ ያለው የፍላጎት ግፊት፡ በሰውነት ውስጥ መነሣሣቱ፥ ቀጥሎ፡ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን ለማድረግ እስከመሻት በሚያደርስ የፍቅር ስሜት መፈቃቀዱና ለጋብቻ መብቃቱ፥ በመጨረሻም፡ ሩካቤ ሥጋን መፈጸሙና በፅንስ ፍሬ መደምደሙ ነው።

ያም፡ የድርጊት ሥርዓታዊ ኺደት፡ በኹለንተናዊ መልኩና ይዘቱ፡ መልካም እንጂ፡ ክፉ፥ ጽድቅ እንጂ፡ ኃጢአት እንዳልኾነ ነው። "ብፁዓን፡ እለ ተኀድገ ሎሙ ኃጢአቶሙ፤ ወእለ፡ ኢሓሰበ ሎሙ፡ ኵሎ ጌጋዮሙ። ብፁዕ ብእሲ፡ ዘኢኈለቈ ሎቱ፡ እግዚአብሔር ኃጢአቶ፤ ወዘአልቦ ጽልሑት፡ ውስተ ልቡ።"

"ኃጢአታቸው፡ ይቅር የተባለላቸው፥ በደላቸውም ኹሉ የተተወላቸው፡ ቡሩኮች ናቸው። በልቡ፡ ተንኰል የሌለበት፥ ከዚህም የተነሣ፡ እግዚአብሔር፡ ኃጢአቱን የማይቈጥርበት ሰው፡ ቡሩክ ነው።" የሚለው፡ የእግዚአብሔር ቃል የተነገረው፡ እንደእነዚህ ላሉት መኾኑን፡ ማስተዋል ይገባል። (መዝ. ፴፩፥ ፩-፪።)

ምናልባት ግን፡ "የለም! ኃጢአት ነው!" ብሎ በእየራሱ የሚያስብ ሰው ቢኖር እንኳ፡ ያም እኮ፡ ቀድሞም፡ በብሉይ ኪዳኑ፥ በይበልጥም፡ በሳዲስ ኪዳኑ፡ በእግዚአብሔር አብና በእኔ፡ በድንግል ማርያም ልጅ፡ በኢየሱስ መሢሕ ቤዛነት በተገኘው የንስሓ ስርየት፡ ለአንዴና ለዘለዓለሙ ተወግዷል።

ስማቸውና ዝክረ ነገራቸው፡ ከዚህ በላይ የተወሳው ቅዱሳንና ቅዱሳት፥ እነርሱን የመሰሉትም ሰዎች ኹሉ፡ ይህን፡ በክፉዎች ዘንድ፡ "ኃጢአት ነው!" ተብሎ የተፈረጀውን፡ ማናቸውንም ድርጊት፥ እዚህ ላይ የምንነጋገርበትን፡ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን ጭምር፡ ሲፈጽሙት እኮ፡ እግዚአብሔር የሠራው፡ የተፈጥሮ ሥርዓት ስለኾነ፡ "መልካምና የጽድቅ ምግባር ነው!" ብለው እንጂ፡ "ኃጢአት ነው!" ብለው አይደለም።

ይህ እውነታ፡ አበክሮና አጠንክሮ የሚያስገነዝባችሁ፡ አንድ ቍም ነገር አለ፤ ይኸውም፡ ማንኛውም፡ ሰብአዊ ፍጡራችን፡ በተቃወሰ አስተሳሰቡ፡ "ጽድቁን፡ 'የለም! ይህ፡ ኃጢአት ነው!' ካለ፡ በእርሱ ዘንድ፡ ያ ጽድቅ፡ ኃጢአት ይኾናል!" የሚለውን፡ ዘይቤ ነው። ቀድሞም ኾነ ዛሬ፡ ብዙዎች፡ የዚሁ ዘይቤ ተጠቂዎች ኾነው ተቀብለውት፡ ሲሠቃዩበት፡ ይኸው፡ በገሃድና በስፋት ይታያል።

እንግዲህ፡ በሰብአውያን ፍጡሮቻችን ዘንድ፡ የነገሮችና የኹኔታዎች አካኼድ፡ መንገዱ፡ ይህ ከኾነ፡ በቅኑም ኾነ በጠማማው ዘንድ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ወሳኙ ኃይል፡ "የሰው አስተሳሰብ እንጂ፡ እውነታው አይደለም!" የሚያሰኝ ይኾናል።

ስለዚህ፡ ክፉዎች፡ "ኃጢአት ነው!" ያሉትን ጽድቅ፡ ደጎች ደግሞ፡ "የለም! ኃጢአት አይደለም!" ብለው፡ ልክ፡ በዚሁ መልክ፡ በጤናማውና በትክክለኛው አስተሳሰባቸው፡ በዚያው በጽድቅነቱ ባሕርይ አጽንተው፡ ሊኖሩበትና ሊፈጽሙት ይቻላቸዋል፤ ይገባቸዋልም። አዎን! ስማቸውና ዝክረ ነገራቸው፡ ከዚህ በላይ የተወሳው ቅዱሳንና ቅዱሳት ያደረጉትም፡ ይኼንኑ ነው።

በዚህ መሠረት፡ እግዚአብሔርን መስሎና አኽሎ የሚወለደውን፥ "ሰው" የሚባለውን ሕያው ፍጡር የሚያስገኘው፥ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል፡ በጋብቻ ኾነ ከጋብቻ ውጪ የሚደረገው፡ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት፡ ያለእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ፥ ያለመለኮታዊው ምክንያትና ዓላማም፡ በተግባር ተፈጽሞ፡ እውን አይኾንም። ያለእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ፥ ያለመለኮታዊው ምክንያትና ዓላማም፡ ያ ሰው፡ መጀመሪያ፡ ዘር ኾኖ፡ በወንዱ አብራክ ውስጥ አይፈጠርም፤ ቀጥሎ፡ የወንዱና የሴቲቱ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት፡ ደርሶ ሊፈጸም፥ የወንዱ ዘር፡ በወር አበባዋ ጠርቶና ለስልሶ፡ ዘሩን ለመቀበል በተዘጋጀው በሴቲቱ ማሕፀን አይፀነስም።

ስለዚህ፡ መፈጠሩና መፀነሱ፡ እንዲህ በሚገለጥበትና በሚታወቅበት፡ በዚህ ኸል ላይ፡ ምንም ዓይነት ጉዳት እንዳይደርስ፡ ኹለታችሁም፡ ወንዱም፥ ሴቲቱም ልጆቻችን፡ ብርቱ ጥንቃቄን ማድረግ ይኖርባችኋል፤ በተባዕትነትና በእንስትነት ጾታ ለይተን የምንሠይመው ያ ዘር፥ ያ ፅንስ፥ ያ ኸል፡ የእግዚአብሔር አብና የእኔ የእግዚአብሔር እም ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም ልጅ፥ ነጋሢና ካህን ነውና! እነዚህ የጸጋ ማዕርጋቱም፡ በቅድሚያ፡ በወንዱ አብራክ ውስጥ ባለው ዘር፥ ከዚያ፡ በሴቲቱ ማሕፀን ውስጥ በተፈጠረው ፅንስ ላይ፡ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፥ ጥምቀትና ቅብዓት፡ ለአንዴና ለዘለዓለም ታትመዋልና።

ከዚህ የተነሣ፡ በእናንተ በባለአደራዎቹ ወንድና ሴት ልጆቻችን ላይ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ የሚያስከትለው የኃላፊነት ተጠያቂነት፡ በዚያው መጠን፡ እጅግ ከባድ ነውና፡ የሰውኛና ሰይጣናዊ በኾነው፡ በ"ወሊድ ቍጥጥር" ሰበብ፡ በዚህ ሽል ላይ፡ ከፅንሱ ጀምሮ፡ ጉዳት እንዳይደርስ፡ አዎን! አንተ፡ ባለዘሩ ወንዱ ልጃችን እና አንቺ፡ ባለፅንሷ ሴቷ ልጃችን፡ ለዚያ ፅንስ፥ ለዚያ ሽል፡ ልዩ ጥንቃቄንና ሙሉ እንክብካቤን ልታደርጉ ይገባችኋል።

እንግዴህ፡ ልጆቼ! ብዙ ጠንቆችን እያስከተለ ያለውን፡ ሰዎች የሠሩትን፡ "የወሊድ ቍጥጥር"ን አማሳኝ ዘዴ ትታችሁ፡ ዘለዓለማዊ ጸጋና በረከት የመላበትን የቍጥጥሩን መለኮታዊ ሥልጣን፡ የሰብአዊው ልደት ፈጣሪና ከዋኝ ለኾነው፡ ለቸሩ አምላካችሁ፡ ለልዑል እግዚአብሔር እና ለእኔ ተዉልን!

## ቅዱሱ ኪዳን፡
## በዚህ ረገድ፡ ያቀረበው፡ ሉዓላዊ ጥሪ።

"የወሊድ ቍጥጥርን" ጠንቅ ካመጡት ምክንያቶች አንዱ፡ ፀረ-እግዚአብሔር የኾኑ፡ እምነተ ቢስ ሰዎች፡ በእየራሳቸው፡ ሓሳዊ አእምሮ ውስጥ የፈጠሩት፡ የሴለና ምትሓት የኾነው፡ ሰይጣናዊው አስተሳሰብ፡ የደካሞችን ቀልብ ስቦ፡ ለዚያ ጎጂ አስተሳሰብ ተገዦች እንዲኾኑ ሊያደርጋቸው በመቻሉ ነው።

እነዚህ እምነተ-ቢስ ሰዎች፡ ረቂቁን እና ግዙፉን መንፈሳዊ እና ሥጋዊ ዓለማት፡ "እምኀበ አልቦ፡ ኀበ ቦ" ፡ "ካለመኖር ወደመኖር" አምጥቶ ያስገኘው እግዚአብሔር፡ በመልኩ ፈጥሮ፡ ይኸው ፈጣሪው፡ "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" ብሎ፡ የራሱ ብቻ የኾነውን፡ የመጨረሻውን የክብር ዘውድ ያቀዳጀውን ሰው፡ "የለም! ከዝንጀሮ የተገኘ ነው!" ብለው፡ ባመነጩት ፍልስፍናቸው፡ ራሳቸው፡ በክፋቱ መንፈስ ተለክፈው፡ አብዛኛውን ሰብአዊ ፍጡራችንን፡ በዚሁ የክፋት መንፈሳቸው የተጠናወቱት የሰይጣን ወገኖች ናቸው።

በፈቃዳቸውና በምርጫቸው፡ እየራሳቸውን፡ ከእኛ ወላጅነት በመለየታቸው፡ ይህ የክፋት መንፈስ የተጠናወታቸው ሰብአውያን ወገኖች፡ "በጋብቻም ኾነ ከጋብቻ ውጪ፡ በልጆች መወለድና በብዛታቸው መጠን ረገድ፡ በግለሰብ፥ በቤተሰብና በኅብረተሰብ ላይ የሚደርሰውን፥ ባዕዳኑና ዘመኑ ያመጡትን፡ ከባድና የተለያየ ብዙ ችግር፡ ልንቋቋመው ስለማንችል፡ መፍትሔው፡ ‹የወሊድ ቍጥጥር› ነው!" ብለው የወሰኑ በመኾናቸው፡ ይኸው፡ በዚሁ ዘዴ አምነውበት፡ የሚፈጽሙት ኾኖ፡ እነሆ፡ በይፋ ሲሠራበት ትመለከታላችሁ።

ይህም የኾነው፡ እነዚሁ የክፉው ወገኖች፡ እግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች የሰጠውን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውን በመካድ ነው። የካዱት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖትም፡ ልጆች፡ ያለእግዚአብሔር ፈቃድና ፈጣሪነት እንደማይወለዱ፥ ሲወለዱም፡ የእግዚአብሔር አብ እና የእኔ፡ የእግዚአብሔር እም ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም ልጆች፥ የመንግሥታችን ነጋሢዎች ወራሾችና አገልጋዮች ካህናት ኾነው እንደሚወለዱ፥ ከዚህ የተነሣም፡ በሕፃናቱም ኾነ፥ በሥጋ ወላጆቻቸው ዘንድ፡ በመለኮታዊው በረከትና ጸጋ፡ የተትረፈረፉቸው ኾነው ከሚኖሩ በቀር፡ በነፍሳዊው እውቀትና ጥበብ፥ በሥጋዊው ገንዘብና ንብረት፥ በመንፈሳዊው ሥልጣንና ኃይልም በኩል፡ ምንም የሚያጡት ነገር ሳይኖር፡ ፍላጎታቸው ኹሉ ተሟልቶ፡ ህልውናቸውን በመልካም እንደሚቀጥሉ የሚያረጋግጠው እምነት ነው።

እንግዴህ፡ እውነታው ይህ ከኾነ፡ በምድርና በሰማያት ሰፍና፡ ፍጥረተ ዓለሙን የምትመራውና የምትጠብቀው፥ የምታስተዳድረውና የምትመግበው፡ ይህች፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ራሷን፡ ለዓለሙ ኹሉ የሰው ልጆች፡ በአዋጅ የገለጠችው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** ዓለም፡ ከተፈጠረ ጀምሮ ስታደርግ እንደኖረችውና ዛሬም እያደረገች እንዳለችው፥ ወደፊትም፡ በዚሁ መልኩና ይዘቱ እንደምትቀጥለው ኹሉ፡ በዚህ፡ በ"ወሊድ ቍጥጥር" እና ከእርሱ ጋር በተያያዙ ጠንቆች ተማርካችሁ ለምትሠቃዩ ግለሰቦች፣ ባለትዳሮችና ቤተሰቦች፥ ኅብረተሰቦችና ብሔረሰቦች ልጆቼ! የምትላችሁን ስሙ!

"ሥጋዊዉን፥ ነፍሳዊዉንና መንፈሳዊዉን ጤናችሁንና ሕይወታችሁን፥ ሰላማችሁንና ደስታችሁን የሚያቃውሰውን፡ ይህን፡ "የወሊድ ቍጥጥር" የምታደርጉት፡ ስለምትወልዷቸው ልጆች መብዛትና ማነስ፡ ቍጥጥር ለማድረግ ብቻ ሳይኾን፡ ሌሎች፡ እጅግ ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩዋችሁ ይችላሉ፤ እነርሱንም፡ እዚህ ላይ መዘርዘሩ፡ የሚያስፈልግ አይኾንም። ምክንያቶቹና ሰበቦቹ፡ የቱንም ያህል የበረከቱ ይኹኑ፡ ለኹሉም፡ እኛ፡ የሰማዩ አባታችሁና የሰማይዋ እናታችሁ፡ መፍትሔውን እናደርጋለን።

"በዚህ፡ የአባትነት እና የእናትነት ጥሪያችን መሠረት፡ በጋብቻም ኾነ ከጋብቻ ውጪ የተፀነሱና የተወለዱ፥ ወደፊትም፡ የሚፀነሱና የሚወለዱ ቢኖሩ፥ የምታደርጉትም ሩካቤ ሥጋ፡ በፈቃዳችሁም ኾነ ያለፈቃዳችሁ የተፈጸመና የሚፈጸም ቢኾን፡ ያለእኛ ፈቃድ የሚኾን፡ ምንም ነገር የለምና፥ ሕፃናቱም፡ ያለእኛ ፈጣሪነት አይፈጠሩምና፥ ከተፈጠሩም፡ እኛ የፈጠርናቸው፡ ለበጎ የሕይወት ዓላማ ነውና፥ ለእነርሱም፡ ምንጊዜም የሚያስፈልገው ኹሉ፡ በምድር ላይ ተዘጋጅቶና ተሟልቶ እንዲገኝ አድርገናልና፡ እባካችሁ! በምንም ዓይነት ዘዴና መንገድ፡ <u>አታስወርዷቸው! ፅንሱንም አትከልክሉ!</u>

"የፈጠርናቸው፡ እርሱ እግዚአብሔር፡ አባታቸው ነውና፥ እኔም፡ ድንግል ማርያም፡ የዘለዓለም እናታቸው ነኝና፥ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ የሚያስፈልጋቸውንም ኹሉ፡ እነሆ፥ አኹንም፥ ምንጊዜም፡ በምድር ላይ አዘጋጅተን እንጠብቃለንና፡ እነርሱን፡ ለእኛ፡ በሰማይም፥ በምድርም፡ ሰፍና፡ መላውን ፍጥረቷን ለምታስተዳድረው፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ስጡን!

በምድር ስፋቷ ላይ መልተው፥ በገጠርም፡ በከተማም፡ በያለበት ሠፍረው የሚኖሩት፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ልጆቻችን፡ ገና በፅንስ ደረጃ ያለውን፥ ሊወለድ የቀረበውንና አኹን የተወለደውን ሕፃን፡ ከነነፍሰ-ጡሯ፥ ከነዐራሷና ከነእመጫቷ ለመቀበል፡ እጆቻቸውን ዘርግተው ሊቀበሏችሁ፡ በየአካባቢያችሁ፥ በየአጠገባችሁና በየውስጣችሁ፡ ይኸው ቆመው፡ እየተጠባበቋችሁ ይገኛሉ።

እነርሱን፡ ፅንሱን እና/ወይም፡ ሕፃኑን ብቻ አይደለም፤ እናንተም፡ ለእነርሱ ፅንሰት፡ ምክንያቶችና መሣሪያዎች የኾናችሁት፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችን ጭምር፡ በችግር ላይ ከኾናችሁ፡ እናንተም፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችንና ዜጎቻችን፥ ነጋሢዎቻችንና ካህናቶቻችን ናችሁና፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ቤታችን የኾነው ፍጥረተ ዓለሙ፡ ቤታችሁ፥ ሀብታችን፡ ሀብታችሁ፥ መንግሥታችን፡ መንግሥታችሁ ናቸውና፡ ወደእኛ ኑና ዐብራችሁን ኑሩ!

ይህ ጥሪያችን፡ እናንተ፡ "አሳዳጊ ያጡና የሙት ልጆች፥ በሥጋ የወለዷቸውን የማያውቁና ችግረኞች የኾኑ ልጆች ናቸው!" ለምትሏቸው፥ ደግሞም፡ የእነርሱ ባለአደራዎች ለኾናችሁትና ለተቸገራችሁት ትልልቆች ኹሉ ነውና፡ ለእናንተም ጭምር፡ እርሱ እግዚአብሔር አባታችሁ፥ እኔም፡ ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም፡ እናታችሁ ነንና፡ እናንተም፡ እንደኪዳናውያቱና እንደኪዳናውያኑ ልጆቻችን ኹሉ፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችንና ዜጎቻችን፥ ነጋሢዎቻችንና ካህናቶቻችን ናችሁና፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ቤታችን የኾነው ፍጥረተ ዓለሙ፡ ቤታችሁ፥ ሀብታችን፡ ሀብታችሁ፥ መንግሥታችን፡ መንግሥታችሁ ናቸውና፡ እናንተም፡ እንደሕፃናቱ፡ ወደእኛ ኑና ዐብራችሁን ኑሩ!

"ይህ የጥሪ መልእክታችን የተላለፈላችሁና ቃላችንም በተግባር ላይ የሚውለው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። አኹን የምትኖሩባትን ምድር ጨምሮ፡ በፍጥረተ ዓለሙ መልታና ሰፍና ያለችውን፡ እርሷንም፡ ከጥንት መሥርተን የምንመራትና የምናስተዳድራት፥ የምንጠብቃትና የምንመግባት፡ እኛ ነን። ከዚህ የልዕልና ምስፍናዋና የህልውና ምልዓቷ የተነሣ፡ በኪዳናውያትና በኪዳናውያን ልጆቻችን አማካይነት፡ እዚያው፡ እናንተው ዘንድ፡ በእያንዳንዳችሁ ውስጥና በአካባቢያችሁ፡ በእውንነቷና በሕያውነቷ ተገልጣ ታገኟታላችሁ። እኛም፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ አጠገባችሁ ኾነን፡ እያነጋገርናችሁ ነን።

"በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት በኩል፥ በቅርቡ የላክንላችሁን፥ የዐዋጅ ቃላችንን ተከትላችሁ፥ እየራሳችሁን፥ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁና በእውነተኛው መንፈስ ቅዱሳዊ አምልኳችሁ አስተካክላችሁና አጽንታችሁ፥ ለእግዚአብሔራዊው ምንነታችሁና ማንነታችሁ አብቅታችሁ ስትገኙ፥ እኛንም፥ በቀጥታ፥ እዚያው፥ በየአካባቢያችሁና በየአጠገባችሁ፥ በየመካከላችሁና በየውስጣችሁ፥ በእውን ታገኙናላችሁ። በዚያን ጊዜና ከዚያ በኋላ፥ የምትፈልጉትና የሚያስፈልጋችሁ ኹሉ፥ እዚያው በየአካባቢያችሁና በየአጠገባችሁ፥ በየመካከላችሁና በየውስጣችሁ፥ ቀርቦላችሁ ታገኙታላችሁ።

"የዚችው፥ ኢትዮጵያ፥ የእግዚአብሔር መንግሥታችን አገልጋዮች ካህናት፥ ለእናንተም፥ ኪዳናውያን ወንድሞቻችሁና ኪዳናውያት እኅቶቻችሁ የኾኑ ልጆቻችንና ነጋሢዎቻችን፥ በየአቅራቢያችሁ አሉና፥ ከእኛም፥ ከእነርሱም ጋር በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኳችሁ አማካይነት ከምታደርጉት ቀጥተኛ ግንኙነት ጋር፥ በዚህ የኅዋ መድረክ፥ በሌላውም መገናኛ መስመር፥ መነጋገርና መጻጻፍ፥ መላላክና መገናኘት ትችላላችሁ። በእነርሱም አማካይነት፥ የእኛ የኾነው መልእክት፥ ለእናንተ፥ የእናንተ የኾነውም፥ ለእኛ ሊተላለፍና ሊደርስ ይችላል።

"ይኼን፥ የዘለዓለም አባታችሁን፥ የእግዚአብሔርን እና የእኔን፥ የዘለዓለም እናት አገራችሁ ኢትዮጵያን፥ የፍቅር ጥሪ ሰምታችሁና ተቀብላችሁ ለመፈጸም ወደኋላ አትበሉ! አታመንቱ! አታወላውሉ! አትጠራጠሩ!

"እናንተ፥ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውና ምግባራቸው፥ እውነተኞችና ጠንካሮች የነበሩት፥ በነቢያትም ቃል፥ "ብፁዕ ሕዝብ፥ ዘእግዚአብሔር አምላኩ! ሕዝብ ዘኀረየ ሎቱ ለርስቱ!" ፥ "እግዚአብሔርን፥ አምላኩ ያደረገ፥ እግዚአብሔርም፥ ርስቱ ያደረገው ሕዝብ፥ ምስጉን ነው!" የተባሉ፥ የእነዚያ፥ የቀደሙት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን ትውልድ ስለኾናችሁ፥ የእነርሱን፥ የታማኝነትና የጽናት ባሕርይ፥ እናንተም መልሳችሁ ወርሳችሁ ያዙ! ለዘለቄታው የሚበጃችሁ፥ እርሱ ነውና! (መዝ. ፴፪፥ ፲፪።)

"በእውነተኛ ፈቃዳችሁና ምርጫችሁ፥ በምትፈጽሙት ንስሓችሁ፥ እየራሳችሁን፥ ለዚህ የሕይወት ጸጋ አብቅታችሁ እስክናገኛችሁ ድረስ፥ አይዟችሁ፥ የእኛ የቃል ኪዳን ጥበቃ፥ ሰላምና ፍቅር፥ ምንጊዜም አይለያችሁም።"

\+ \+ \+

ተዐውደ፥ በመጋቢት ፲፮ ቀን፥ ፳፻፯ ዓመተ ምሕረት ታወጀ።

ላእከ ኢትዮጵያ፥ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፣
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፣
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
ስመ ጥምቀቱ፥ ኂሩተ-ወልድ።